# በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን

ኢኮሥኮ
ECWC
የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን
ETHIOPIAN CONSTRUCTION WORKS CORPORATION

## የወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ

## እና

## የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ማንዋል ቁጥር 018

ሀምሌ/2011ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማ ው ጫ

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

*1.1. አጭር ርዕስ* ..........................................................................................5

*1.3. የማንዋሉ የአፈጻጸም ወሰን* ...........................................................................7


## ክፍል ሁለት

## 2. የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የአፈፃፀም ሂደት_Toc15723696

*2.1. የሥራ ዕድል ፈጠራ መንገዶች፡-*..........................................................................9

*2.4.የሥራ እድል ፈጠራ ቅንጅታዊ አሰራር አፈጻጸም ሂደት*............................................10

*2.6.የቀጥታ ጊዜያዊ ቅጥር ሥርዓት አፈፃፀም ስርአት፡-* ....................................................10

*2.7. የጊዜያዊ ቅጥር ጥሪ ስለማስተላለፍ ስርአት፡-* ............................................................11

*2.8. የጊዜያዊ ሰራተኞች የስራ እድል ፈጠራ ምልመላና ማስረጃ ምዝገባ ሥርዓት፡-*.............12

*5/ የጊዜያዊ ቅጥር መረጣ ሥርዓትና መረጃ ማደራጀት*......................................................13

*6/ ለጊዜያዊ ቅጥር የተመረጡት ስራ ፈላጊዎችን ወደ ሥራ ስለማስገባት ሥርአት፡-*............14

*7/ ዋስትና ስለማቅረብ*...................................................................................15


## ክፍል ሶስት

## 3. ለቋሚ ኢንተርፕራይዞ በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ስለማሰማራት

## የሚፈጠር የስራ እድል አሰራር ሥርዓት (Sub-contracting)

*3.1. የቅድመ ዝግጅት ስራዎች የስራ ሂደት ስርአት፡-*........................................................15

*3.2. ከአካባቢ አስተዳደር የመቀናጀት አሰራር ስርአት፡-*...................................................16

*3.3. የኢንተርፕራይዝ መረጃ የማደራጀትና የመመዝገብ አሠራር ስርአት፡-*..........................16

*3.4. የኢንተርፕራይዞች መረጃ ማደራጀት፣ መረጣና ማጽድቅ ሥርዓት፡-*...........................17

*3.5. የተመረጡ ኢንተርፕራይዞችን ወደ ሥራ የማስገባት ሥርዓት፡-*.................................18

*3.6. የሪፖርት ዝግጅትና የውል ማቋረጥ ስርአት፡-* ........................................................18

3.7ለቋሚ ኢንተርፕራይዞች ..........................................................................................19

3.8 *ሥራዎችን በንዑስ ተቋራጭነት የማስተላለፍ ሥራ ፍሰት*(Sub-contracting) ...............19

## ክፍል አራት

## *4. በውክልና ሥለሚሰጡ ሥራዎች የአፈጻጸም ስርአት*

*4.1. የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን የማከናወን ስርአት፡-* ....................................................21

*4.2. በውክልና እንዲሰሩ የተመለመሉ ኢንተርፕራይዞች  ምዝገባ ስርአት፡-* .........................22

4.*3. የተመለመሉ ኢንተርፕራይዞችን ማስረጃ የማጣራት፣የመምረጥና የማፅደቅ ሂደት፡-*.......23

4.*4.ለኢንተርፕራይዞች የስራ/የሽያጭ ውክልና መስጠትና ወደ ሥራ ስለማስገባት ሂደት፡-*.....23

## *ክፍል አምስት*

## በኮንትራት ስለሚሰጡ አሰራሮች

5.1 ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች  በኮንትራት ስለሚሰጡ ስራዎች .............................................26

5.2 የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን የማከናወን ስርአት፡-......................................................................26

5.3. በኮንትራት እንዲሰሩ የተመለመሉ ኢንተርፕራይዞች  ምዝገባ ስርአት፡- .......................................27

5.4. የተመለመሉ ኢንተርፕራይዞችን ማስረጃ የማጣራት፣የመምረጥና የማፅደቅ ሂደት፡-.......................28

5.5. ለኢንተርፕራይዞች ስራውን በኮንትራት የመስጠትና  ወደ ሥራ ስለማስገባት ሂደት፡- ..................28

5.6. የሪፖርት ዝግጅትና የውል ማቋረጥ ስርአት፡-.........................................................................29

## ክፍል ስድስት

## ለኢንተርፕራይዞች ስለሚተላለፉ የስራ አይነቶች


1)ከትራንስፖርት መሰረተ ልማት ዘርፍ ሥራ አኳያ........................................................32

2) ከህንጻ ቴክኖሎጂ ዘርፍ ስራዎች አኳያ------------------------------------------------------------------32

3) ከውሃ መሰረተ ልማት ዘርፍ ሥራዎች አኳያ............................................................34

4) ከኮንስትራክሽን መሰራሪያዎች ማንጅመንት ዘርፍ ስራዎች አኳያ-------------------------------------34


## ክፍል ሰባት

## የአስፈፃሚ አካላት እና ሚናዎቻቸው


7.1. ዋና ዋና አስፈፃሚ አካላት..........................................................................35

(ለ) የዋና ዋና አካላት ሚናቸው፡-...........................................................................36


## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች


8.1. በኢንተርፕራዞች ስለሚቀርብ ቅሬታ-----------------------------------------------------------41

8.2. ስለተከለከሉ ተግባራት--------------------------------------------------------------------------41

8.3 የአሰራር ማንዋሉ ስለሚጸናበት ገዜ-------------------------------------------------------------41

8.4. ማንዋሉን ስለማሻሻል---------------------------------------------------------------------------42

## መግቢያ

ባለፉት ዓመታት የወጣቱን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ተሣትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ በተለይም የመጀመሪያውን የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻ በማድረግ በተዘጋጀው የወጣቶች የልማትና ዕድገት ፓኬጅ መሠረት ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ወጣቶች የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ችለዋል፡፡ በተለየም በኮንስትራክሽን ዘርፉ በተለያዩ የሙያና የቀን ሥራዎች ላይ በርካታ ወጣቶች እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩት ኢንተርፕራይዞች ሚና ኢንዱስትሪው አሁን ለደረሰበት የእድገት ደረጃ የነበራቸው አስተዋጽዎ ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡

ሆኖም እንደ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን አይነት ግዙፍ ፕሮጀክቶች የሚያንቀሣቅሱ ተቋማት ለበርካታ ወጣቶች ሠፊ የስራ እድል መፍጠር ቢችሉም ብቃት ያለው መረጃ ለሚመለከተው የመንግስት አካል/ ኤጀንሲ/ ያለማስተላለፍ፣ የተሟላና የጠራ መረጃ ያለመያዝ፣ ፕሮጀክቶቹ በሚካሄድባቸው የአካባቢ የአስተዳደር መዋቅር ጋር በተገቢው ያለመቀናጀት፣ ወጥነት ያለው አሠራር ያለመከተል፣ የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘረጋውን አሠራር ያልተከተለ መሆን፣ የኢንተርፕራይዝ ፈጠራና የመደበኛ የሠራተኛ ቅጥር በተገቢው መለየት አለመቻል፣የሥራ እድል ፈጠራ ተግባርን ከዋናው አላማ ጋር በአስተሳሰረ መንገድ ያለመፈፀም ወዘተ ዋነኛ ችግሮች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም በግዙፍ ፕሮጀክቶች በጊዜያዊነት የሚፈጠሩ የሥራ ዕድል ተሣታፊዎችና ተጠቃሚዎች ጥሪት አፍርተው ወደ ቋሚ የሥራ ዕድል እንዲሸጋገሩ የሚደረገውም ድጋፍ ውስን ነው፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ችግሮችን በሂደት ደረጃ በደረጃ መፍታት እንዲያስችለው ይህንን የአሠራር ማንዋል ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### *1.1. አጭር ርዕስ*

ይህ የአሰራር መመሪያ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን "የኢኮስኮ የወጣቶች የስራ ዕድል ፈጠራና የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ማንዋል" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1.2. የቃላት ትርጉም

ለቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጣቸው በስተቀር በዚህ መመሪያ መሰረት፡-

(1) "የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ" ማለት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሕጋዊነትን በማስፈን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚሰጡ አገልግሎቶች እና የመንግስታዊ ድጋፎችና አገልግሎቶች በተቀናጀ መልኩ ከአንድ ስፍራ በአንድ አስተባባሪ አካል ሥር ካሉ አካላት የሚያገኙበት አደረጃጀት ነው፡፡

(2) "ከተማ" ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም 2 ሺህ ወይም ከዚያ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚያ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡

(3) "ስራ ፈላጊዎች" ማለት ዕድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ ሆኖ ከ60 ዓመት ያልበለጡ ቋሚ የገቢ ምንጭ የሌላቸው የሀገሪቱ ዜጎች ሁሉ ማለት ነው፡፡ የመስራት ፍላጎትና ችሎታ እያላቸው የራሳቸውን ሥራ በመፍጠርም ሆነ በመቀጠር ቋሚ የሥራ መስክ የሌላቸው፤ ያልተማሩትንና በተለያየ የትምህርት ደረጃ የሚገኙ ወገኖች ሁሉ ሥራ ፈላጊዎች ተብለው ይመዘገባሉ፡፡

(4) የዩንቨርሲቲና የኮሌጅ ምሩቃን ሥራ ፈላጊዎች" ማለት ከመንግስትና ከግል ዩኒቨርሲቲዎች በዲግሪና ከዚያ በላይ፤ ከመንግስትና ከግል ኮሌጆች፣ የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት ከደረጃ I-V የተመረቁና በዘርፉ የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ፍላጎት ያላቸው ማለት ነው፡፡

(5) "የሥራ ዕድል ፈጠራ" ማለት የመስራት አቅም እያላቸው በተለያየ ምክንያት ወደ ስራ ያልገቡ ዜጎችን በጊዜያዊ ወይም በቋሚ የስራ ዘርፎች ማሠማራት ነው፡፡

(6) “ቋሚ የሥራ ዕድል” ማለት የራሳቸውን ኢንተርፕራይዝ ፈጥረው የሚሰሩ ወይም በሌሎች ድርድቶች ውስጥ ተቀጥረው ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪ በመሆን በፔይሮል ክፍያ በማግኘት የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ማለት ነው፡፡

(7) “ጊዜያዊ የሥራ ዕድል” ማለት በጥሪት ማፍሪያ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች/ በጊዜያዊነት የራሳቸውን ኢንተርፕራይዝ አቋቁመው ወይም በማናቸውም ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ከአንድ ዓመት ላነሰ ጊዜ ክፍያ ለማግኘት የተሰማሩ ከሆነ ጊዜያዊ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ማለት ነው፡፡

(8) “የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ” ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞት ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 (ሃምሣ ሺህ) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,000(አንድ መቶ ሺህ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡

(9) “አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ” ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣ የቤተሰብ አባላት ተቀጣሪ ሰራተኞች ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000(ሃምሣ ሺህ) እስከ 500,000 (አምስት መቶ ሺህ) ወይም በከተማ ግብርና፣ በባህላዊ ማዕድን ማምረትና በግንባታ ዘርፍ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) እስከ 1.5 ሚሊዮን ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡

(10) “ነባር ኢንተርፕራይዝ” ማለት ሕጋዊ ሰውነት ወይም ፈቃድ አግኝተው አንድ ዓመት እና ከዛ በላይ የሞላቸው ሲሆኑ ሲቋቋሙ የተሟላ ወይም /በከፊለ የድጋፍ አገልግሎት ያገኙ ወይም ያላገኙ ሊሆኑ ይችላሉ፣

(11) “አዲስ ኢንተርፕራይዝ” ማለት በኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት መሠረት ሕጋዊ ፈቃድ አግኝተው ወደ ሥራ ከተሰማሩ አንድ ዓመት ያልሞላቸው ሲሆኑ ሲቋቋሙ የተሟላ ወይም በከፊል የድጋፍ አገልግሎት ያገኙ ወይም ያላገኙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

(12) ”ባለድርሻ አካላት” ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት በገጠር የወረዳ/የቀበሌ አስተዳደር አካላት፣በከተማ የአንድ ማእከል አገልግሎት አስተባባሪዎች እና የስራ እድል ፈጠራና የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን ይመለከታል፡፡

(13) "ተቋም" ማለት በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የኮርፖሬሽኑ መዋቅር ላይ የሚገኝ ሆኖ ለስራ ፈላጊዎች በቀጥታ የስራ ትስስር የሚያደርግ/የሚፈጥር ወይም ስራዎችን የሚያስተላልፍ አካል ነው፡፡

(14) "ቅንጅት " ማለት የኮርፖሬሽኑ ዘርፎች፣መመሪያዎች፣ዲስትሪክቶች፣ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች እርስ በእርስ እንዲሁም የስራ እድል በመፍጠር ዙሪያ ኃላፊነት ያለባቸው የአከባቢ የአስተዳደር አካላት እና በዚህ መመሪያ በግልጽ የተጠቀሱትን የፌዴራል የመንግስት ተቋማት ከስራ እድል ፈጠራ እቅድ ጀምሮ እስከ አፈጻጸም የማጠቃለያ ግምገማ ስራ ድረስ በጋራና በመናበብ የሚሰሩትን ስራ የሚመለከት ነው፡፡

15) "አመቻች" ማለት የስራ ፈላጊዎችን መረጃ በመያዝ በኮርፖሬሽኑ የስራ ዕድል ሲፈጠር ከኮርፖሬሽኑ ጋር ግንኙነት የሚያደርግ የከተማ ወይም የገጠር ከተማ ወረዳ ቀበሌ አስተዳደር ነው፡፡

### *1.3. የማንዋሉ የአፈጻጸም ወሰን*

ይህ የአሰራር መመሪያ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በተዋረድ በሚገኙ አደረጃጀቶች እና በዚህ መመሪያ መሰረት ግልጽ ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላትን አተገባበርን ብቻ የሚመለከት ነው፡፡

### *1.4. አጠቃላይ ዓላማ፣ዝርዝር አላማዎች፣ ትርጓሜዎችና መርሆዎች*

#### 1/. አጠቃላይ ዓላማ

የወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራን በየአካባቢው ከሚገኙ የአስተዳደር አካላትና የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጋር ማቀናጀት የሚያስችል ያሰራር ስርዓት በመዘርጋት ለወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠርና የኮርፖሬሽኑን ተልዕኮ የተሣካ ማድረግ ነው፡፡

#### 2/. ዝርዝር ዓላማዎች

(ሀ) በኮርፖሬሽኑ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች፣ በዲስትሪክት ቅ/ጽ/ቤቶችና በተለያዩ ፕሮጀክቶች ለሥራ ፈላጊዎች የሚተላለፍ ሥራዎች በተደራጀና በተቀናጀ መረጃ ተደራጅቶ የሚያዝበት፣ሥራዎችም ግልጽነትን በተላበሰ አግባብ ለስራ ፈላጊዎች የሚተላለፍበትና ወጥ በሆነ መንገድ ሪፖርቶች ለሚመለከታቸው አካላት የሚተላለፍበት ሥርዓት መዘርጋት መቻል ነው፤

(ለ) ከኮርፖሬሽኑ የሥራ ባህሪ አኳያ በየአካባቢው ቅንጅታዊ አሰራር መዘርጋት መቻል ማለትም ፕሮጀክቶች ካሉበት አካባቢ የሚገኙ የወረዳ ወይም የቀበሌና የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጋር ማቀናጀት የሚቻልበት ስልት መዘርጋት ነው፤

(ሐ) ለሥራ ፈላጊዎች የሚተላለፉ ስራዎች በመንግስት የአሰራር ስርአት መሰረት እና ከኮርፖሬሽኑ የስራ ባህሪ አኳያ ያሉትን የስራ እድል አማራጮች አተገባበር በኢንተርፕራይዝ ደረጃ፣ በጊዜያዊ ቅጥር እና በዉክልና/በሽያጭ ውክልና/ ስርዓት መሰረት በግልፅ ተለይቶ የሚያዝበትና በዚሁ መሠረት የድጋፍ ክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ ተለይቶ የሚፈጸምበት ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

**3/ መርሆዎች**

(ሀ).ለሥራ ፈላጊዎች የሚተላለፉ ሥራዎች መሠረታዊ የኮርፖሬሽኑን መመሪያዎችና አሠራሮች የተከተለ፣ ግልፅነትን የአሣታፊነትና የወጥነት መርህን በጠበቀ መንገድ የሚፈፀሙ መሆናቸውን መረጋገጥ አለበት፡፡

(ለ). ለሥራ ፈላጊዎች የሚተላለፉ መሠረታዊ ሥራዎች ውጤቶች በምንም ሁኔታ ቢሆን ጥራትን ያላጐደሉ/ መሆናቸውን የተረጋገጠ መሆን አለባቸው፤በሂደቱ ችግሮች ባጋጠሙ ወቅት ኮርፖሬሽኑ ለሥራው ስኬታማነት አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ የማስተካከል ሙሉና ቀጥተኛ ኃላፊነት አለበት፡፡

(ሐ).ለኢንተርፕራይዞች በቋሚነት የሚተላለፉት ስራዎች በቅድሚያ ከዩኒቨርሲቲና ከኮሌጅ ለተመረቁ ወጣቶችና ሴቶች ስለመሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

(መ).በሙያ ተደራጅተው የሚመጡ ሥራ ፈላጊዎች በቂ ስልጠና የወሰዱ፣ የኮርፖሬሽኑን መመዘኛዎች ያሟሉና ብቁነታቸው በልቀት ማዕከል (COC) የተረጋገጠላቸው መሆን አለባቸው፡፡

(ሠ). በሥራ ዕድል ፈጠራው ሂደት የሴቶች ተሣትፎና ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን የማረጋገጥ ሥራ መከናወን ይኖርበታል፡፡

(ረ). የሥራ እድል ፈጠራ ስራው በተቻለ መጠን የህዝብ ግንኙነት ስራ እንዲታጀብ የማድረግ የአሰራር መርህን መከተል አስፈላጊ ይሆናል፡፡

(ሰ) የስራ እድል ፈጠራ ስራ ቅንጅት በቀዳሚነት የሚጀምረው ከእቅድ ጀምሮ ሁሉንም የሚመለከታቸው አካል ያሳተፈ መሆኑን ማረጋገጥ የሚገባ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## 2. የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የአፈፃፀም ሂደት

### *2.1. የሥራ ዕድል ፈጠራ መንገዶች፡-*

ከኮርፖሬሽኑ የስራ ባህሪ አንጻር የወጣቶች የስራ እድል ፈጠራ በአራት መንገድ በመለየትና በማደራጀት መከናወን መቻል አለበት፡፡ እነዚህም፡-

(ሀ) በቀጥታ በጊዜያዊ ቅጥር ፤

(ለ) በንዑስ ተቋራጭነት( Subcontracting)፤

(ሐ) የሽያጭ ወኪል በመሰየም፤ እና

(መ) ኮንትራት በመስጠት ይሆናል፡፡

### *2.2. የስራ እድል ፈጠራ ስራ እቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም*

ማናቸውም የኮርፖሬሽኑ ፕሮጀክቶች ወይም አገልግሎቶች ወይም ምርቶች በሚዘጋጁበት፣በሚታቀዱበት እና ወደ ተግባር በሚገባበት ወቅት በወጣት ስራ አጥ ወጣቶች እና ሴቶች እንዲሁም ባለሙያዎች መተግበር የሚችሉ ስራዎች ተለይቶ እንደአግባብነቱ ከላይ በተገለጸው አማራጭ ስራ እድል መፍጠሪያ ዘዴዎች እንዲሆን ታሳቢ መደረግ አለበት፡፡ በተጨማሪም የስራ እድል ፈጠራ እቅድ ዝግጅትና መረጃ ማደራጀት፣ማስተላለፍ ስራ ከኮርፖሬሽኑ የስራ እቅድ ጋር በተቀናጀ መንገድ በኮርፖሬሽኑ ዕቅድ እንዲካተት በኮርፖሬሽኑ መመሪያ በተወሰነው የማቅረቢያ የግዜ ሰሌዳ እና ከዚህ ጋር በአባሪ በተያያዘው ቅጽ መሰረትና ተጨማሪ መግለጫ በሴቶች፣ ወጣቶችና ሕፃናት ጉዳይ መምሪያ ተዘጋጅቶ ለስትራተጂክ ማኔጅመንትና እቅድ መምሪያ በበጀት

አመት መጀመሪያ መተላለፍ ይኖርበታል። በተጨማሪም ከፌዴራል የምግብ ዋስትናና ስራ ዕድል ፈጠራ ኤጀንሲ በተላከውና ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው የዕቅድ ቅጽ መሰረት ከዘርፎች አስፈላጊ መረጃዎችን በመሰብሰብ የሥራ ዕድል ፈጠራ ዕቅድ በሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ የሚዘጋጅ ይሆናል።

### 2.3. የስራ እድል ፈጠራን የሚከታተል ባለሙያ ስለመመደብ

የስራ ቦታው ያለበት የኮርፖሬሽኑ የስራ ኃላፊ የስራ እድል ፈጠራን የተግባር እንቅስቃሴ ከስራው ጋር በማቀናጀት የሚከታተል ባለሙያ የመመደብ ኃላፊነት አለበት። የዚህንም አፈጻጸም ሂደት ዘርፎች የመከታተል እና ለሚመለከታቸው ኃላፊ የማሳወቅ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም በሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ የስራ ዕድል ፈጠራ ዕቅድና አፈጻጸም የሚከታተል ባለሙያ መመደብ ይኖርበታል።

### 2.4.የሥራ እድል ፈጠራ ቅንጅታዊ አሰራር አፈጻጸም ሂደት

የስራ እድል ቅንጅታዊ ስራ አፈጻጸም የሚጀምረው በዋነኛነት ከስራ አይነት መለየት፣ ማሳወቅ፣ማስጸደቅና እና የጸደቀውን በአመታዊ የስራ እድል ፈጠራ እቅድ ላይ የሚመለከታቸውን በማግባባትና በማዘጋጀት እና በጋራ በመስራት የሚወሰን መሆን አለበት።

### 2.5. የስራ እድል ፈጠራ እቅድ ዝግጅት አፈጻጸም

የስራ እድል ፈጠራ እቅድ ዝግጅትና መረጃ ማደራጀት፣ማስተላለፍ ስራ ከኮርፖሬሽኑ የስራ እቅድ ጋር በተቀናጀ፣በኮርፖሬሽኑ መመሪያ በተወሰነው የማቅረቢያ የግዜ ሰሌዳ እና ከዚህ ጋር በአባሪ በተያያዘው ቅጽ መሰረትና ተጨማሪ መግለጫ ተዘጋጅቶ ለስትራተጂክ ማኔጅመንትና እቅድ መምሪያ በበጀት አመት መጀመሪያ መተላለፍ ይኖርታል።

### 2.6.የቀጥታ ጊዜያዊ ቅጥር ሥርዓት አፈፃፀም ስርአት፡-

(ሀ) የጊዜያዊ ቅጥር ፍላጐት ከፕሮጀክት፣ ከዲስትሪክት ጽ/ቤቶች ለሚመለከተው ዘርፍ በየዓመቱ በተዘጋጀው ቅጽ የማስተላለፍ ሥራ መሥራት መቻል አለበት፤

(ለ) ዘርፎች በተገቢው አደራጅተው በዝርዝር ዕቅድና የድርጊት መርሃ ግብር ፕሮግራም መሠረት ለዋናው መ/ቤት ለሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ እና ለኮርፖሬት ስትራቴጂክ ማኔጅመንትና እቅድ መምሪያ ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል፤

(ሐ) የኮርፖሬት ስትራቴጂክ ማኔጅመንት እና እቅድ መምሪያ በሚመለከተው አካል በማስፀደቅ ለሥራ ዕድል ፈጠራና ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እንዲላክ ያደርጋል፤

(መ) የጊዜያዊ ሥራዎች ቅጥር ሙሉ በሙሉ ውክልና በተሰጠው እና ሥራው ባለበት አካባቢ ባለው የኮርፖሬሽኑ ተቋም ይፈጸማል፡፡

(ሠ) ውክልና የተሰጠው የኮርፖሬሽኑ ተቋም ለጊዜያዊ ሥራ ዕድል ፈጠራ ቅጥር በዚህ መመሪያ መሠረት በአቅራቢው ከሚገኘው በከተማ ከሆነ ከአንድ ማዕከል አስተባባሪው በገጠር ከሆነ ከቀበሌና ከወረዳ አስተዳዳሪ ጋር በመቀናጀትና አስቀድሞ በማሣወቅ በፕሮግራም እንዲመራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

(ረ) በኮርፖሬሽኑ በጊዜያዊነት የሚሣተፉ ወጣቶችና ሴቶች ሁኔታን ለመለየት የሚያስችል መመዘኛ የማዘጋጀት፣የማደራጀት ስራ ማከናወን ይገባል፡፡

(ሰ) የሥራ መመዘኛው በየዓመቱ ከሥራ ባህሪ በመነሣት ልዩ የሚያደርገውን በመለየት የሚያዘጋጀው በሚመለከተው ዘርፍ አማካኝነት ሆኖ በስትራቴጂክ ማኔጅመንት ኮሚቴ/በማኔጅመንት መፅደቅ ይኖርበታል፡፡

### *2.7. የጊዜያዊ ቅጥር ጥሪ ስለማስተላለፍ ስርአት፡-*

የጊዜያዊ ቅጥር ጥሪ በቀጥታ የሚተላለፈው በአቅራቢያው ለሚገኘው የመንግስት መዋቅር ሲሆን የሚከተሉትን ግምት ያስገባ ይሆናል፡-

(ሀ) የኮርፖሬሽኑን የአሰራር መመሪያዎች ሥርዓት የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ፤

(ለ) በዝርዝር ዕቅድና የድርጊት መረሃ ግብር የተደገፈ መሆኑን፤

(ሐ) የቅጥሩ ሁኔታ፤

(መ) በቅጥሩ መሣተፍ የሚገባቸው አካላት መስፈርት፣

(ሠ) የሚያስፈልገው ቅጥር ለየትኛው የሥራ ዓይነት እንደሆነ፣

(ረ) የስራው ልዩ አካባቢና የሚያስፈልገው ሰው ብዛት፣

(ሰ) ሥራው የሚፈልገው የፆታና የሙያ ሁኔታን ግምት ውስጥ ያስገባ፣

(ሸ) ሥራው የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት የግዜ ግምት፣

(ቀ) ከብዛት አኳያ ለማወዳደር እንዲያስችል በሚመለከተው አስተዳደር አካል መመልመል የሚያስፈልገው መጠን መግለጽ፤

(በ) የቅጥር ማስታወቂያ የሚተላለፈው በፅሁፍ ሲሆን የሚመለሰው በዚሁ አግባብ መሆኑን ማመላከት ይኖርበታል፡፡

### *2.8. የጊዜያዊ ሰራተኞች የስራ እድል ፈጠራ ምልመላና ማስረጃ ምዝገባ ሥርዓት፡-*

#### *1/ ስለ ጊዜያዊ ቅጥር ሰራተኞች ምልምላ*

የግዜያዊ ስራ እድል ቅጥር ስራ አጥ ወጣቶችና ሴቶች ምልመላና መረጃ የሚተላለፈው በአካባቢው ባለው የአስተዳደር መዋቅር አመራር አካላት አማካኝነት ብቻ ነው፡፡

#### *2/ ስለ ጊዜያዊ ቅጥር ሰራተኞች የምዝገባ ማስረጃ*

(ሀ) የጊዜያዊ ሰራተኞች የስራ እድል ፈጠራ ምዝገባ የስራ እድል የሚፈጠረው የስራ አካባቢ ገጠር ከሆነ ከወረዳው ወይም ከቀበሌው የአስተዳደር አካል የተላከ የምልመላ ማስረጃ ይሆናል፣ ወይም

(ለ) ሥራው የሚገኝበት ከተማ ከሆነ ከቀበሌ/ከክፍለ ከተማው የአንድ ማእከል አገልግሎት የተላከ ለስራ እድል ፈጠራ የተመለመሉ ወጣቶችንና ሴቶች የሚያመለክተው ማስረጃ መሆን አለበት፤

#### *3/ ማስረጃን ስለማጣራት*

(ሀ) ከወረዳ/ከቀበሌ ወይም ከአንድ ማእከል አገልግሎት የተላከው ማስረጃ ተቋሙ በላከው መመዘኛ መሰረት እጩ ሰራተኞች/ ስራ ፈላጊዎች የተመለመሉ ስለመሆኑ፣

(ለ)የምልመላው ስራ ግልጸኝነትና አሳታፊነትን ያረጋገጠ ሰለመሆኑ ማስታወቂያዎችና ቃለጉባኤ መያያዙን ማረጋገጥ፣

(ሐ)የተላከው ማስረጃ አግባብ ባለው ኃላፊ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

#### 4/ የምልመላ ማስረጃ ምዝገባና ክትትል

(*ሀ) በመዝገብ ስለመያዝ*

ከአካባቢው አስተዳደር አካል የሚላከው የጊዜያዊ ቅጥር ማስረጃ በቋሚ መዝገብ ወይም በኮምፒውተር በኤክስኤል ተመዝግቦ በአስተማማኝ መልኩ ባክ አፕ እየተያዘ መፈፀም

ይኖርበታል፡፡ በምዝገባ ሂደቱም የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡-

*(ለ) በፕሮጀክት/ዲስትሪክት የተመደበ ባለሙያ የስራ ኃላፊነት*

1) ባለሙያው ስራውን በተገቢው እንዲወጣ ይህንን መመሪያ እና ሌሎች የኮርፖሬሽኑ መመሪያዎችንም ግምት ውስጥ ያስገባ ኦረንቴሽን የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

2) የሚመደበው ባለሙያ የስራ እድል የሚፈጠርበትን የስራ መስክ ግምት ባስገባው እቅድ መሰረት ተገቢውን የድርጊት መርሃግብር ተከትሎ ምዝገባውን ስራ በብቃት መወጣት ይኖርበታል፡፡

3) ባለሙያውም ሲመዘግብ የሚከተሉትን በዝርዝር የማጣራት ኃላፊነት አለበት፤-

i) ከሚመለከተው የመንግስት አስተዳደር አካል የተላከው በጥሪው መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ፣

ii) ማስረጃው የተላከበት ጊዜና ሁኔታ የሚገልጽ (በማን ተላከ፣ በማን ኃላፊ ተረጋገጠ፣ በቃለጉባዔ የተያዘበት በማህተም፣ መረጃ መኖሩን....)

iii) የምዝገባ ሂደት የቅደም ተከተልን መርህ የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ፣

iv) የምዝገባ ሂደቱ በተቀመጠው የአሰራር ሂደት መሠረት ስለመሆኑና በቅርብ ኃላፊ እንዲመዘገብ የተመራበት መሆኑን የማረጋገጥ፣

*(ሐ) የምዝገባ ሂደትና ክትትል*

i).ምዝገባ እንደአግባብነቱ በየቀኑ መከናወን መቻል አለበት፤

ii).የቅርብ ኃላፊ ቢያንስ በሶስት ቀን አንድ ጊዜ ስለትክክለኛነቱ የማረጋገጥና የማጽደቅ ሥራ ማከናወን መቻል አለበት፡፡

### *5/ የጊዜያዊ ቅጥር መረጣ ሥርዓትና መረጃ ማደራጀት*

(ሀ) የመረጣ ሥርዓቱ የተሻለ ግልፅነት ለመፍጠር የሚመለከተው አስተዳደር ተወካይ ያሣተፈ እንዲሆን ማድረግ (ቀድሞ ቀኑን ፕሮግራሙን የማሣወቅ) ይገባል፤

(ለ) የመጨረሻውን ማስረጃዎች የማጣራትና የመምረጥ ሥራ ላይ ከአስተዳደሩ ኃላፊ ወይም የአንድ ማእከል አገልግሎት ኃላፊ(ተወካይ) በተጨማሪ ቢያንስ የተቋም ኃላፊን ጨምሮ ሶስት አባላት እንዲኖሩት በማድረግ መስራት መቻል አለበት፤

(ሐ) የምርጫው ስርዓት በተዘጋጀው መመዘኛ መሠረት ሆኖ ዝርዝር ምክንያቶች የያዘና በቃለ ጉባዔ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፤

(መ) በሚዘጋጀው ቃለ-ጉባዔ ለየትኛው ሥራ የትኛው ስራ ፈላጊ እንደሆነና ከመቼ እስከ መቼ ድረስ ሊሰራ እንደሚችል በግልፅ የተመለከተ መሆን አለበት፤

(ሠ) ቃለ ጉባኤው በኮርፖሬሽኑ የቃለጉባኤ አጻጻፍ(የጥራት ስራ አመራር አሠራር) መሠረት የሚያዝ ሆኖ ከቋሚ መዝገቡ ወይም በኮምፒውተር ኤክስኤል ከተያዘው ጋር እንዲናበብ በማድረግ መስራት አለበት፤

(ረ) በቃለ ጉባኤ የፀደቀው የጊዜያዊ ቅጥር ወርና ዓ.ም በባገናዘበ መንገድ በቦክስ ፋይል በሚገባ ተደራጅቶ መያዝ አለበት፡፡

### *6/ ለጊዜያዊ ቅጥር የተመረጡት ስራ ፈላጊዎችን ወደ ሥራ ስለማስገባት ሥርአት፡-*

(ሀ) የተመረጡትን ባለሙያዎች ፈቃደኝነታቸውን እንዲያረጋግጡ ማሣወቅ ያስፈልጋል፡፡

(ለ) የጊዜያዊ ቅጥሩ በኮርፖሬሽኑ ያሰራር መመሪያ መሠረት የጊዜያዊ ቅጥር ውል ማዘጋጀት ይገባል፡፡

(ሐ) በተዘጋጀው ውል መሠረት ተዋዋይ ወገኖች በህጉ መሰረት እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡፣

(መ) ለጊዜያዊ ቅጥሩ በአካል የተገኙት ማስረጃቸው የተላከላቸውና የተመረጡት ስራ ፈላጊዎች ስለመሆናቸው በማረጋገጥ ውል መፈጸም ይገባል፤፡

(ሠ) በኮርፖሬሽኑ አሰራር መሰረት ውሉንም ሆነ ቅጥሩን ለማጽደቅ ውክልና የተሰጠው አካል እንዲፈርምበት ይገባል፡፡

(ረ) ውሉም ቀድሞ ከተዘጋጀው ቃለ-ጉባዔ ጋር ተደራጅቶ የሚያዝ ይሆናል፡፡

(ሰ) የተዘጋጁ ቃለ-ጉባዔዎች ውሎች ቢያንስ በሁለት ኮፒ ለሚቀጥለው የበላይ አካል እንዲተላለፍ መደረግ መቻል አለበት፡፡ አንደኛው ኮፒ በራሱ በተቋሙ መያዝ መቻል አለበት፤

(ሸ) በጊዜያዊነት የሚቀጠሩ ባለሙያዎች ስለ ሥራው ሁኔታና ሥለ ራሣቸው ሚና የሚያስገነዘብ ዝርዝር ኦሪንቴሽን የሚሰጥበት፣ ዝርዝር የአሰራር ዲሲፒሊኖች መብቶቻቸውና ግዴታቸውን እንደ ውሉ በሚገባ የማስገንዘብ ሥራ መሰራት ይገባል፤

(ቀ) በኦረንቴሽኑ በብቃት የተሣተፉተን ሥራውን ለመቀጠል የሚፈልጉ ባለሙያዎች /ጊዜያዊ ተቀጣሪዎች የጊዜ ሰሌዳውን መሠረት ባደረገ መንገድ የማሰማራት የመከታተልና የመደገፍ ሥራ ማከናወን መቻል አለበት፤

(በ) በሂደቱ ፈቃደኛ ያልሆኑና የሚንጠባጠቡ ካሉ ወዲያውኑ ከመጠባበቂያ የመተካት እንደአግባብነቱ ለሚመለከተው የአስተዳደር አካል የማሣወቅና የማስተካት ሥራ ማከናወን ይገባል፡፡

## *7/ ዋስትና ስለማቅረብ*

የጊዚያዊ ቅጥር የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸው ከኮርፖሬሽኑ ጋር ለመስራት ውል የፈረሙ ሰራተኞች በተለይም በጥበቃ ስራዎች ላይ የሚሰማሩ ዜጎች በግል ወይም ካደራጃቸው አካል ዋስትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## 3. ለቋሚ ኢንተርፕራይዞ በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ስለማሰማራት የሚፈጠር የስራ እድል አሰራር ሥርዓት (Sub-contracting)

### *3.1. የቅድመ ዝግጅት ስራዎች የስራ ሂደት ስርአት፡-*

(ሀ) ለኢንተርፕራይዞች ሥራዎችን የማስተላለፍ ሥራ በዝርዝር ዕቅድና የድርጊት መርሃ ግብር የሚመራ መሆኑን የማረጋገጥ ሥራ መሠራት አለበት፤

(ለ) ለኢንተርፕራይዞች የሚተላለፉ ሥራዎች በተገቢው የመለየት፣ የምናሣትፈውን የኢንተርፕራይዝ ብዛት፣ የሥራው ዓይነትና ቦታ በዝርዝር መታወቅና በተገቢው ቅጽ መደራጀት መቻል አለበት፤

(ሐ) የተደራጀው ሥራ ከየትኛው የከተማ ወይም የክልል/የወረዳ አስተዳደር ጋር እንደሚቀናጅ የመለየት ሥራ መሠራት መቻል አለበት፤

(መ) የተደራጀው መረጃና ዕቅድ ለሚመለከተው የዘርፍና የመንግስት አስተዳደር አካል የማስተላለፍ ሥራ ማከናወን፤

(ሠ) በአካባቢው ካለው የከተማ/የወረዳ/የቀበሌ አስተዳደር በፅሁፍ በማሣወቅ የማቀናጀት ሥራ መሠራት አለበት፤

(ረ) ለኢንተርፕራይዝ ሥራ ዕድል ፈጠራን የሚከታተል አንድ ቋሚ ተወካይ መመደብ፤ይህንንም ለሚመለከተው የአካባቢ አስተዳደር አካል ለመረጃ ልውውጥ የማሳወቅ ስራ መስራት መቻል ይኖርበታል፡፡

### 3.2. ከአካባቢ አስተዳደር የመቀናጀት አሰራር ስርአት፡-

(ሀ) የሚመለከተው የፕሮጀክት ኃላፊ ወይም ተወካይ  ከሚመለከታቸው የአካባቢው አስተዳደር መዋቅር አመራር አካላት ጋር በመገናኘት ቋሚ የግንኙነት ጊዜ በመወሰን ለመሥራት መዘጋጀት አስፈላጊ ነው፤

(ለ) ዝርዝር የኢንተርፕራይዝ ፍላጐት መግለጫ ማለትም የኢንተርፕራይዝ ብዛት፣ የሰለጠኑበት ሙያ ስብጥር ሁኔታ፣ የሚተላለፍላቸው የሥራ ዓይነት፣ ሥራው ሊፈጅ የሚችለው ግምታዊ የጊዜ ሰሌዳ ወዘተ የያዘ መሆኑን የሚያመለክትና (የሚጠበቅበትን የጊዜ ሰሌዳ) ወዘተ ለአስተዳደር አካሉ መግለጫ መስጠት፣ ማሳወቅ፣መግባባት መደረስ አለበት፤

(ሐ) በስራው መሰማራት የሚፈልጉ ባለሙያዎች በአስተዳደሩ በኩል ተመልምለው ለፕሮጀክቱ የሚተላለፍበት ግዜና ስርአት በጋራ የመወሰን ስራ መሰራት አለበት፤

(መ) ከአካባቢው አስተዳደር አካል ጋር በተደረሰው ስምምነት መሰረት የኮርፖሬሽኑ የስራ እድል የሚፈጥረው ጽ/ቤት ኃላፊ የምልምላ ስራ ተከናውኖ መረጃው እንዲተላለፍ እንደአግባብነቱ ለሚመለከታቸው የወረዳ/የቀበሌ/ አስተዳደር ወይም የከተማ አስተዳደሩ የአንድ ማእከል አገልግሎት በጽሁፍ ጥሪ ማድረግ አለበት፤

### 3.3. የኢንተርፕራይዝ መረጃ የማደራጀትና የመመዝገብ አሠራር ስርአት፡-

(ሀ) የኮርፖሬሽኑ ዘርፎች ወይም ዲስትሪክት ቅ/ጽ/ቤቶች ወይም ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች የስራ እድል የሚፈጠርላቸውን ኢንተርፕራይዞች በቋሚነት መመዝገብ የሚያስችል መዝገብ ወይም አማራጭ አሰራር መዘርጋት ይኖርባቸዋል፤ ሆኖም የምዝገባ ሂደቱና አሰራሩ ወጥነት እንዲኖረው የአላማ አስፈጻሚ ዘርፎች ማቀናጀት ይጠበቅባቸዋል፤

(ለ) ኮርፖሬሽኑ በሚያዘጋጀው የስራ እድል ፈጠራ መዝገብ ላይ መመዝገብ የሚችለው ኢንተርፕራይዝ ከአካባቢው አስተዳደር ተመልምለው የተላኩትን ብቻ የሚመለከት ነው፤

(ሐ) በስራ እድል ፈጠራው የኢንተርፕራይዝ ዓይነት፣ ብዛት፣ የሥራው ዓይነት፣ የሥራው ቦታ ወዘተ የሚያመላክት ሆኖ የተለየ መዝገብ ወይም በኮምፒውተር በኤክስኤል በተገቢው ባክ አፕ እየተያዘ እንዲሰራ መደረግ አለበት፤

(መ) የኮርፖሬሽኑ ተወካይ ባለሙያ ምዝገባውን ሲካሄድ ግምት ከሚያስገባቸው ማስረጃዎች መካከል ኢንተርፕራይዙ ሲመረጥ የሚመለከታቸው አካላት የተሳተፉበትና የተደራጀ ቃለ ጉባኤ መኖሩን፣በሚመለከተው ኃላፊ በህጋዊ ማህተምና መሸኛ ደብዳቤ መላኩን፣በመመዘኛው መሰረት የኢንተርፕራይዝ አባላት ማስረጃዎች መያያዛቸውን፣የኢንተርፕራይዝ አደረጃጀት ህጋዊ ስርአቱን የተከተለ ስለመሆኑ የሚያመለክቱ ማስረጃዎች መያያዛቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

### 3.4. የኢንተርፕራይዞች መረጃ ማደራጀት፣ መረጣና ማጽድቅ ሥርዓት፡-

***(ሀ)*** ***የ***ኢንተርፕራይዞች ምልመላ መረጃዎች ትክክለኛነት ተረጋግጦ በተላከበት ቅደም ተከተል ራሱን በቻለ ቦክስ ፋይል መደራጀት መቻል አለበት (ወርና ዓ.ም. በያዘ አግባብ)፤

(ለ) የተላከው መረጃና ማስረጃዎች የሚያመለክቱት ሰፊ አማራጭ ወይም ተወዳደሪነት ያለው ከሆነ በመመዘኛው መሠረት ከሚመለከተው አካል ጋር የማወዳደርና የመለየት ሥራ ማከናወን፤

(ሐ) ኢንተርፕራይዞችን በማወዳደር እና በማጥራት ሂደት ግምት ከሚገባው መካከልም በአገሪቱ የሥራ ዕድል ፈጠራ መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን መመዘኛ ያሟሉ ማለትም ህጋዊነት፣ በልቀት ምዘና ማለፋቸው አግባብ ያለው ሥልጠና የወሰዱ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሥራ መሥራት አለበት፤

(መ) ኮርፖሬሽኑ ለስራው የሚያስፈልጉ ባለሙያዎችን ለመለየት ባወጣው መሰረታዊ መመዘኛና ከላይ በዝርዝር በቀረበው የአሰራር ሂደትና መስፈርት መሰረት የተለዩ ኢንተርፕራይዞችን የተቋሙን ኃላፊ ጨምሮ በሶስት አባላት እና የአስተዳደር ተወካይ በተገኙበት የማፅደቅ ሥራ ማከናወን ይገባል፡፡

## 3.5. የተመረጡ ኢንተርፕራይዞችን ወደ ሥራ የማስገባት ሥርዓት፡-

(ሀ) የተመረጡ ኢንተርፕራይዞችን የሚመለከታቸውን በተገቢው ደብዳቤ የሥራ መጀመሪያ፣ የኦረንቴሽን ጊዜን፣ የሥራው ውለታ የሚታሰርበት ወዘተ መረጃ በማስተላለፍ የማሣወቅ ሥራ መሥራት አለበት፤

(ለ) ወደ ሥራ የማስገባት ዝርዝር የድርጊት መረሃ ግብር የማዘጋጀት ሥራ መሥራት፤

(ሐ) ለተመረጡ ኢንተርፕራይዞች ሥራዎችን ለማስተላለፍ የሚያስችል ውለታ የማዘጋጀት የማዋዋል ሥራ መስራት፤

(መ) ወደ ዝርዝር ሥራ ከመግባታቸው በፊት ለአንተርፕራይዞች ዝርዝር የሥራ ኦረንቴሽን መሥጠት መቻል አለበት፤

(ሠ). በውለታውና በኦረንቴሽኑ መሠረት ኢንተርፕራይዞች ወደ ሥራ ማስገባት ይህንንም ለሚመለከታቸው ሁሉ የማሣወቅ ሥራ መሥራት አለበት፤

(ረ) ከኦረንቴሽን በፊትም ሆነ በኂላ ውለታ ያልፈፀሙና ወደ ሥራ መግባት ያልቻሉ ኢንተርፕራይዞችን በቶሎ በተጠባባቂ መተካት ወይም ለሚመለከተው የአስተዳደር አካል በማሣወቅ ተተኪ ኢንተርፕራይዝ እንዲላክ የማድረግ ሥራ መሠራት  ይገባል።

## 3.6. የሪፖርት ዝግጅትና የውል ማቋረጥ ስርአት፡-

(ሀ) ለኢንተርፕራይዞች የተሰጡ ሥራዎች በተጠናቀቀ ጊዜ ዝርዝር ሪፖርት የስራ እድሉን የፈጠረውና ለኢንተርፕራይዞች ፕሮጀክቱ በቀጥታ ያስተላለፈው ተቋም አማካኝነት መዘጋጀት አለበት፤

(ለ) የማጠቃለያ ሪፖርቱም በኮርፖሬሽኑ በኩል ለኢንተርፕራይዞች የተሰጠውን ዝርዝር የስራ አይነት፣ ከኢንተርፕራይዞች ጋር የተደረገው የሥራ ውል ጊዜ፣ የሥራ አፈጻጸም ሂደት፣ ያሣተፈው የኢንተርፕራይዝ ብዛት፣ በኢንትረፕራየዞች አማካኝነት የተፈጠረው የሥራ ዕድል ብዛት፣ ለኢንተርፕራይዙ የፈጠረው  ጠቅላላ ገቢ፣ የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ዋጋ፣ በስራ ዕድል ፈጠራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች ወዘተ መያዙን ማረጋገጥ ይገባል፤ አለበት።

(ሐ) ዝርዝር ሪፖርቱ በየተቋማቱ አማካኝነት ለዘርፎች ተጠቃሎ መተላለፍ አለበት፣ ሪፖርቱም በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ በተደራጀ አግባብ መያዝ አለበት፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ ስራዎች አፈጻጸም መረጃ በሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ከዘርፎች ተሰባስቦና በኤጀንሲው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ መሰረት ተዘጋጅቶ ለኤጀንሲው መላክ ይኖርበታል፡፡

(መ) የውል ማቋረጥ ስራ መደበኛውን የኮንትራት አስተዳደር ውል የአሰራር መርህ ሳይጥስ፣ በቅድሚያ ለኢንተርፕራየዙ ሥራው በተገቢው መጠናቀቁን በማረጋገጥ አስፈላጊውን የውል ማቋረጥ ሥነ-ሥርዓት እንደሚከናወን በማሣወቅ ማከናወን መቻል አለበት፤

(ሠ) ኢንተርፕራይዙ በሥራ ሂደቱ እንደ ውሉ ዝርዝር ሁኔታና የሥራ ስፔሲፊኬሽን መሠረት ማከናወን ካልቻለ፤ ህጉ በሚፈቅደውና በኮንትራት ውሉ ስነ ስርአት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በኮርፖሬሽኑ ላይ የደረሰ ጉዳት ካለ ዝርዝሩን በማካተት ኢንተርፕራይዙን ላደራጀው አካል እንዲሁም ለኢንተርፕራይዙ ዋስትና ለሰጠው አካል ሪፖርት መላክ ይኖርበታል፡፡


## ለቋሚ ኢንተርፕራይዞች

## ሥራዎችን በንዑስ ተቋራጭነት የማስተላለፍ ሥራ ፍሰት(Sub-contracting)

ለኢንተርፕራይዞ ሥራን በንዑስ ተቋራጭነት(Subcontracting) ለማስተላለፍ የሚረዳ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ይከናወናሉ

↓

ከአካባቢው የመስተዳደር አካላት ጋር የመቀናጀት ስራ ማከናወን




## *ክፍል አራት*

### *4. በውክልና ሥለሚሰጡ ሥራዎች የአፈጻጸም ስርአት*

የኮርፖሬሽኑን አገልግሎቶች ወይም ምርቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝነት ለተደራጁ ወጣት ስራ ፈላጊዎች ከሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላት ጋር በመቀናጀት ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተሉትን የስራ ሂደቶችን ተግባራዊ ማድረግ የሚገባ ይሆናል፡፡

### *4.1. የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን የማከናወን ስርአት፡-*

(ሀ) ለኢንተርፕራይዞች በውክልና ሊተላለፉ የሚችሉ ስራዎች ወይም ምርቶችን የመለየት ስራ እንዲከናወን ማድረግ፤

(ለ) ለኢንተርፕራይዞች የሚተላለፉ ሥራዎች በአግባቡ ለመምራት እንዲቻል በተለየው ስራ ላይ ማሳተፍ የሚያስችለውን የኢንተርፕራይዝ ብዛትና አደረጃጀት ሁኔታ፤

(ሐ) ለኢንተርፕራይዞች የሚተላለፈው የሥራው ዓይነትና ቦታ፣የሚተላለፈው ስራ ጠቅላላ ውጪ፣

(መ) የሚተላለፈው ስራ ለኢንተርፕራይዙ ሊያስገኝ የሚችለው የገቢ ግምት መጠን እና ከኢንተርፕራይዞች የሚጠበቁ ግዴታዎች፤

(ሠ) የሚተላለፈው ስራ ተግባራዊ ሂደቱ የሚጀምረው መቼና እንዴት በምን አግባብ እንደሆነ ማመላከት መቻል፤

(ረ) ከላይ የተመለከቱትን እና ሌሎች ዝርዝር ተግባራትን የያዘ እቅድና የድርጊት መርሀግብር ማዘጋጀት፤ለሚመለከተው ከፍተኛ አካል በማቅረብ ማስጸደቅ፤

(ሰ) የጸቀደውን እቅድ ለሚመለከተው የኮርሬሽኑ የስትራተጂክ ማኔጅመንትና እቅድ መምሪያ የማሳወቅ ስራ መስራት፤

(ሸ) በእቅዱ መሰረት ለማስፈጸም የተለየውን ስራ ከየትኛው የከተማ ወይም የክልል/የወረዳ አስተዳደር ጋር እንደሚቀናጅ በማረጋገጥ ለተግባራዊነቱ ተገቢው ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግ በጽሁፍ የማሳወቅ ስራ መስራት ይገባል፤

(ቀ) ግንኙነት ለፈጠረላቸው የአስተዳደር አካላት አግባብ ያለው ኦረንቴሽን በመስጠት ስለ ስራው ሂደትና ቅንጅት ግንዛቤ የማስያዝ ስራ መሰራት አለበት፤

(በ) ሥራው የሚገኝበት ተቋም ለኢንተርፕራይዝ ሥራ ዕድል ፈጠራን ስራ ለማሳካት አግባብ ያለውን ጉዳዩን በቅርብነት የሚከታተል አንድ ቋሚ ተወካይ መመደብ ይጠበቅበታል፣ይህንንም ለሚመለከተው የአካባቢ አስተዳደር አካል ለመረጃ ልውውጥ የማሳወቅ ስራ መስራት መቻል ይኖርበታል፣

(ተ) የውክልና ስራውን ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት አግባብ ያለው የውክልና ውል እንዲዘጋጅ ማድረግ፣በዚሁ አግባብ እንዲፈጸምም ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ኢንተርፕራይዞች ተመልምለው እንዲላኩ በጹሁፍ ጥሪውን ማስተላለፍ አለበት፡፡

## *4.2. በውክልና እንዲሰሩ የተመለመሉ ኢንተርፕራይዞች ምዝገባ ስርአት፡-*

(ሀ) ኮርፖሬሽኑ ከሚያመርታቸው ምርቶች ወይም የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በውክልና ለተወሰነ ጊዜ በኢንተርፕራይዞች አማካኝነት ሊሠሩ የሚችሉ ሥራዎችን ለመለየት የሚያስችል መመዘኛ ማዘጋጀትና የማስጸደቅ ሥራ መሥራት፤በዚሁ አግባብ መላኩን የማረጋገጥ ስራ መስራት፤

(ለ) ኮርፖሬሽኑ በሚያዘጋጀው የስራ እድል ፈጠራ መዝገብ ላይ መመዝገብ የሚችለው ኢንተርፕራይዝ ከአካባቢው አስተዳደር ተመልምለው የተላኩትን ብቻ የሚመለከት ነው፤
(ሐ) በስራ እድል ፈጠራው የኢንተርፕራይዝ ዓይነት፣ ብዛት፣ የሥራው ዓይነት፣ የሥራው ቦታ ወዘተ የሚያመላክት ሆኖ የተለየ መዝገብ ወይም በኮምፒውተር በኤክስኤል በተገቢው ባክ አፕ እየተያዘ እንዲሰራ መደረግ አለበት፤

(መ) የኮርፖሬሽኑ ተወካይ ባለሙያ ምዝገባውን ሲካሄድ ግምት ከሚያስገባቸው ማስረጃዎች መካከል ኢንተርፕራይዙ ሲመረጥ የሚመለከታቸው አካላት የተሳተፉበት የተደራጀ ቃለ ጉባኤ መኖሩን፣በሚመለከተው ኃላፊ በህጋዊ ማህተምና መሸኛ ደብዳቤ መላኩን፣በመመዘኛው መሰረት የኢንተርፕራይዝ አባላት ማስረጃዎች መያያዙን፣የኢንተርፕራይዝ አደረጃጃት ህጋዊነትን የማረጋገጥ ስራ መስራት አለበት፡፡

(ሠ) በማጣራት ሂደት በውክልና የሚተላለፈው ስራ ኮርፖሬሽኑ ከሚያመርታቸው ምርቶች መካከል ኢንተርፕራይዞች ተወክለው ሽያጭ የሚያከናውኑ ከሆነ በቅድሚያ ምርትን ለማከማቸት በቂ መጋዘንና የስራ ቦታ መኖሩን የማረጋገጥና በምዝገባ ሂደት ይህንን የሚመለክት ማስረጃ መያያዙን ማጣራት ይገባል፤

(ረ) በቅርበት ከሚገኘው የአስተዳደር አካል የተላከውን የኢንተርፕራይዝ ማስረጃ ተገቢነት በማረጋገጥ በቋሚ መዝገብ/በኮምፒውተር ባክ አፕ በመመዝገብና በተገቢው በማደራጀት ለቀጣይ ስራ ዝግጁ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

### 4.3. የተመለመሉ ኢንተርፕራይዞችን ማስረጃ የማጣራት፣የመምረጥና የማፅደቅ ሂደት፡-

(ሀ) በኮርፖሬሽኑ መዝገብ ላይ ስማቸው የሰፈሩና ለማጣራት ስራው ያለፉ እንተርፕራይዞች መረጃ እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሁሉም የሚመለከተው አካልና ኢንተርፕራይዞች በቅድሚያ እንዲያውቁት የማድረግ ስራ መሰራት ይኖርበታል (ለምሳሌ በመለጠፍ…)፤

(ለ) በአቅራቢያው ከሚገኘው አካል በውክልና ለመሥራት ብቁ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን መረጃ በተገቢው ቃለ-ጉባዔ የተደገፈ መሆኑን ፣ መረጃውም ትክክለኛ መሆኑን በድጋሚ የማረጋገጥ ሥራ መሥራት፤

(ሐ) የተላኩ ኢንተርፕራይዞች ኮርፖሬሽኑ ያዘጋጀውን መመዘኛ የሚያሟሉ መሆኑን በማጣራት የአካባቢው አስተዳደር ተወካይ ያለበት ሆኖ የኮርፖሬሽኑ የሥራው አካባቢ የቅርብ ኃላፊ ጨምሮ ሶስት አባላት ባለው ቃለ-ጉባዔ ተይዞ እንዲፀድቅ ይደረጋል፡፡ ሆኖም የአካባቢው ተወካይ መገኘት ባልቻለ ግዜ የተቋም ኮሚቴ አባላት ይወስናሉ፤

(መ) የተመረጡትና የጸደቀላቸው ኢንተርፕራይዞች መረጃ ቃለ-ጉባዔ ከምልመላው ቃለ-ጉባዔና ሌሎች መረጃዎች ጋር ተደራጅቶ የሚያዝ ይሆናል፡፡

### 4.4.ለኢንተርፕራይዞች የስራ/የሽያጭ ውክልና መስጠትና ወደ ሥራ ስለማስገባት ሂደት፡-

(ሀ) በውክልና ሥራው የሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ስለመመረጣቸው በፅሁፍ እንዲያውቁ የማድረግ ስራ መስራት፤በመመዘኛው መሰረት የሚጠበቅባቸውን መራጃዎች እንዲያቀርቡ የማስገንዘብ ስራ ማከናወን፤

(ለ) የውክልና (የሽያጭ) ውል በቅድሚያ የማዘጋጀት ሥራ የማከናወን፣በሚመለከተው ክፍል የማስጸደቅና አደራጅቶ የመያዝ ተግባር መፈጸም፤

(ሐ) ለተወካይ ኢንተርፕራይዝ ውለታ እንዲፈጽሙ ጥሪ የማስተላለፍ፣ ዝርዝር የውል ማሥረጃውም በማሥገንዘብ ውለታ እንዲገቡ የማድረግ ሥራ መሥራት፤

(መ) የውክልና ማስረጃዎች ቢያንስ በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ ለአሠሪው፣ ለሚቀጥለው የዘርፍ ክፍል እና ለተወካይ የሚተላለፍበት ሥርዓትና ( እንደአግባብነቱ ህግ በሚፈቅደው መሠረት የውልና ማስረጃ ምዝገባ ሥርዓት የሚከተል ሊሆን ይችላል) ሁኔታ ማመቻቸት፤

(ሠ) የውክልናው ሥራ ዝርዝር አካሄድ ወይም ዝርዝር አፈጻጸም ሂደት በተገቢው የድርጊት መርሃ ግብርና በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ይፈፀማል፡፡ ሆኖም ዝርዝር አፈፃፀም ሂደቱ ውክልና የተሰጠበት የገንዘብ መጠን ለኢንተርፕራይዙ የተሰጠ ሥራ የሚያስገኘው የገቢ መጠን፣ የፈጠረው የሥራ ዕድልን በአካተተ አግባብ መሆኑ መረጋገጥ ይገባዋል፡፡

## *<u>በውክልና ሥራዎችን የመስጠት የሥራ ፍሰት</u>*

*ሥራዎችን በውክልና ለመስጠት የሚረዳ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ይከናወናሉ*

በውክልና እንዲሰሩ ኢንተርፕራይዞችን የመመልመል እና የመመዝገብ *ሥራ*

የተመለመሉ ኢንተርፕራይዞችን ማስረጃ የማጣራት፣ የመምረጥና የማጽደቅ ስራ

*ለኢንተርፕራይዞች የስራ/የሽያጭ ውክልና መስጠትና ወደ ሥራ የማስገባት ስራ*

*ለኢንተርፕራይዞች የተፈጠረ የሥራ ዕድል ሪፖርት ማድረግ*

## *ክፍል አምስት*

## በኮንትራት ስለሚሰጡ አሰራሮች

### *5.1 ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች  በኮንትራት ስለሚሰጡ ስራዎች*

*ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች  በኮንትራት ስለሚሰጡ ስራዎች ማለት የኮርፖሬሽኑ የፋሲሊቲ መምሪያ ወይም በዚ ደረጃ በየዘርፍ የሚገኙ ድጋፍ ሰጪ አካላት በተለያዩ የጉልበት ስራ ወይም የግቢ ጥገና ስራ ወይም የጽዳት ስራ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ የስራ አይነቶችን ስራው በሚገኝበት አካባቢ ወረዳ ወይም ከተማ ወይም ገበሬ ማህበር የአመራር አካላት ጋር በመቀናጀት ለቋሚ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በኮንትራት እንዲሰሩ የሚሰጥበት ስርአት ነው፡፡*

### *5.2 የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን የማከናወን ስርአት፡-*

*(ሀ) ለኢንተርፕራይዞች በኮንትራት ሊሰሩ የሚችሉ ስራዎችን የመለየት ስራ እንዲከናወን ማድረግ፤*

*(ለ) ለኢንተርፕራይዞች በኮንትራት እንዲሰሩ በተለየው የስራ ላይ ማሳተፍ የሚያስችለውን የኢንተርፕራይዝ ብዛትና አደረጃጀት ሁኔታ ማወቅ፤*

*(ሐ) ለኢንተርፕራይዞች በኮንትራት እንዲሰሩ የሚፈለገው የሥራው ዓይነትና ቦታ፣የሚተላለፈው ስራ ጠቅላላ ወጪ፣*

*(መ) የሚተላለፈው ስራ ለኢንተርፕራይዙ ሊያስገኝ የሚችለው የገቢ ግምት መጠን እና ከኢንተርፕራይዞች የሚጠበቁ ግዴታዎች መወሰን/ለምሳሌ ዋስትና/፤*

*(ሠ) የሚተላለፈው ስራ ተግባራዊ ሂደቱ የሚጀምረው መቼና እንዴት በምን አግባብ እንደሆነ ማመላከት መቻል፤*

*(ረ) ከላይ የተመለከቱትን እና ሌሎች ዝርዝር ተግባራትን የያዘ እቅድና የድርጊት መርሀግብር ማዘጋጀት፤ለሚመለከተው ከፍተኛ አካል በማቅረብ ማስጸደቅ(ለዋና ስራ አስፈጻሚ ወይም ከስራ የገንዘብ መጠን ግምት በመነሳት ለዘርፍ ኃላፊ)፤*

(ሰ) የጸቀደውን እቅድ ለሚመለከተው የኮርሬሽኑ የስትራተጂክ ማኔጅመንትና እቅድ መምሪያ የማሳወቅ ስራ መስራት፤

(ሸ) በእቅዱ መሰረት ለማስፈጸም የተለየውን ስራ ከየትኛው የከተማ ወይም የክልል/የወረዳ ወይም የገበሬ ማህበር አስተዳደር ጋር እንደሚቀናጅ በማረጋገጥ ለተግባራዊነቱ ተገቢው ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግ በጽሁፍ የማሳወቅ ስራ መስራት ይገባል፤

(ቀ) ግንኙነት ለፈጠረላቸው የአስተዳደር አካላት አግባብ ያለው ኦረንቴሽን በመስጠት ስለ ስራው ሂደትና ቅንጅት ግንዛቤ የማስያዝ ስራ መሰራት አለበት፤

(በ) ሥራው የሚገኝበት ተቋም ለኢንተርፕራይዝ ሥራ ዕድል ፈጠራን ስራ ለማሳካት አግባብ ያለውን ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተል አንድ ቋሚ ተወካይ መመደብ ይጠበቅበታል፣ይህም ተወካይ የኮንትራት ስራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ስራውን በቅርበት የመከታተል ኃላፊነት አለበት፤ እንደአግባብነቱ ከሚመለከተው የአካባቢ አስተዳደር አካል መረጃ መለዋወጥ ይኖርበታል፤

(ተ) የስራ አይነት፣መጠን፣የሚያስፈለገው የገንዘብ መጠን፣የስራው መጠናቀቂያ ግዜ ወዘተ የያዘ የስራ ውል ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት ማዘጋጀት አለበት።
(ቸ)በዚሁ አግባብ እንዲፈጸምም ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ኢንተርፕራይዞች ተመልምለው እንዲላኩ በጹሁፍ ጥሪውን ማስተላለፍ አለበት። እንደአግባብነቱ ኢነተርፕራዞች እርስ በእርስ እንዲወዳደሩ እድል መፍጠር ይጠበቅበታል፤፡

## 5.3. በኮንትራት እንዲሰሩ የተመለመሉ ኢንተርፕራይዞች ምዝገባ ስርአት፡-

(ሀ) ኮርፖሬሽኑ በኮንትራት ሊያሰራ ስለፈለገው ስራ ሁኔታ ብቁ ሊሆኑ ስለሚችሉ የተደራጁ ኢነተርፕራይዞችን ለመለየት የሚያስችል መመዘኛ ማዘጋጀትና የማስጸደቅ ሥራ መሥራት፤በዚሁ አግባብ ከሚመለከተው አስተዳደር አካል መላኩን የማረጋገጥ ስራ መስራት፤

(ለ) ኮርፖሬሽኑ በሚያዘጋጀው የስራ እድል ፈጠራ መዝገብ ወይም የመረጃ መያዣ ላይ መመዝገብ። የሚመለዘገቡትም ኢንተርፕራይዞች ከአካባቢው አስተዳደር ተመልምለው የተላኩትን ብቻ የሚመለከት ነው፤

(ሐ) በስራ እድል ፈጠራው የኢንተርፕራይዝ ዓይነት፣ ብዛት፣ የሥራው ዓይነት፣ የሥራው ቦታ ወዘተ የሚያመላክት ሆኖ የተለየ መዝገብ ወይም በኮምፒውተር በኤክስኤል በተገቢው ባክ አፕ እየተያዘ እንዲሰራ መደረግ አለበት፤

(መ) የኮርፖሬሽኑ ተወካይ ባለሙያ ምዝገባውን ሲካሄድ ግምት ከሚያስገባቸው ማስረጃዎች መካከል ኢንተርፕራይዙ ሲመረጥ የሚመለከታቸው አካላት የተሳተፉበት የተደራጀ ቃለ ጉባኤ መኖሩን፣በሚመለከተው ኃላፊ በህጋዊ ማህተምና መሸኛ ደብዳቤ መላኩን፣በመመዘኛው መሰረት የኢንተርፕራይዝ አባላት ማስረጃዎች መያያዙን፣የኢንተርፕራይዝ አደረጃጀት ህጋዊነትን የማረጋገጥ ስራ መሰራት አለበት።

## *5.4.* የተመለመሉ ኢንተርፕራይዞችን ማስረጃ የማጣራት፣የመምረጥና የማፅደቅ ሂደት፡-

(ሀ) በኮርፖሬሽኑ መዝገብ ላይ ወይም አግባብ ባለው የኮምፒተር መረጃ መሰረት ስማቸው የሰፈሩና ለማጣራት ስራው ያለፉ እንተርፕራይዞች መረጃ  እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሁሉም የሚመለከተው አካልና ኢንተርፕራይዞች በቅድሚያ እንዲያውቁት የማድረግ ስራ መሰራት ይኖርበታል(ለምሳሌ በመለጠፍ...)፤

(ለ) በአቅራቢያው ከሚገኘው ለኮንትራት ስራው ብቁ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን መረጃ በተገቢው ቃለ-ጉባዔ የተደገፈ መሆኑን ፣ መረጃውም ትክክለኛ መሆኑን በድጋሚ የማረጋገጥ ሥራ መሥራት፤

(ሐ) የተላኩ ኢንተርፕራይዞች ኮርፖሬሽኑ ያዘጋጀውን መመዘኛ የሚያሟሉ መሆኑን በማጣራት የአካባቢው አስተዳደር ተወካይ ያለበት ሆኖ የኮርፖሬሽኑ የሥራው አካባቢ  የቅርብ ኃላፊ ጨምሮ ሶስት አባላት ባለው ቃለ-ጉባዔ ተይዞ እንዲፀድቅ ይደረጋል። ሆኖም የአካባቢው ተወካይ መገኘት ባልቻለ ግዜ የተቋም ኮሚቴ አባላት ይወስናሉ፤

(መ) የተመረጡትና የጸደቀላቸው ኢንተርፕራይዞች መረጃ ቃለ-ጉባዔ ከምልመላው ቃለ-ጉባዔና ሌሎች መረጃዎች ጋር ተደራጅቶ የሚያዝ ይሆናል።

## *5.5.* ለኢንተርፕራይዞች ስራውን በኮንትራት የመስጠትና  ወደ ሥራ ስለማስገባት ሂደት፡-

(ሀ) ለኮንትራት ስራው ኢንተርፕራይዞች ስለመመረጣቸው በፅሁፍ እንዲያውቁ የማድረግ ስራ መስራት፤በመመዘኛው መሰረት የሚጠበቅባቸውን መራጃዎች እንዲያቀርቡ የማስገንዘብ ስራ ማከናወን፤

(ለ) የኮንትራት የስራ ውል በቅድሚያ የማዘጋጀት ሥራ የማከናወን፣በሚመለከተው ክፍል የማስጸደቅና አደራጅቶ የመያዝ ተግባር መፈጸም፤

(ሐ)በኮንትራት ስራውን እንዲያከናውን ለተመረጠው ኢንተርፕራይዝ ውለታ እንዲፈጽሙ ጥሪ የማስተላለፍ፣ ዝርዝር የውል ማሥረጃውም በማሥገንዘብ ውለታ እንዲገቡ የማድረግ ሥራ መሥራት፤

(መ) የኮንትራት ስራ ውል ማስረጃዎች ቢያንስ በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ ለአሠሪው፣ ለሚቀጥለው የዘርፍ ክፍል እና ለተወካይ የሚተላለፍበት ሥርዓትና ( እንደአግባብነቱ ህግ በሚፈቅደው መሠረት የውልና ማስረጃ ምዝገባ ሥርዓት የሚከተል ሊሆን ይችላል) ሁኔታ ማመቻቸት፤

(ሠ) የኮንትራት ሥራ ዝርዝር አካሄድ ወይም ዝርዝር አፈጻጸም ሂደት በተገቢው የድርጊት መርሃ ግብርና በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ይፈፀማል፡፡

## 5.6. የሪፖርት ዝግጅትና የውል ማቋረጥ ስርአት፡-

(ሀ) ለኢንተርፕራይዞች የተሰጡ ሥራዎች በተጠናቀቀ ጊዜ ዝርዝር ሪፖርት የኮንትራት ስራው እንዲከናወን ውል የገባውና ያስፈጸመው አካልያደረገው ዝርዝር ሪፖርት መዘጋጀት አለበት፤

(ለ) የማጠቃለያ ሪፖርቱም በኮርፖሬሽኑ በኩል ለኢንትርፕራይዞች የተሰጠውን ዝርዝር የስራ አይነት፣ ከኢንተርፕራይዞች ጋር የተደረገው የሥራ ውል ጊዜ፣ የሥራ አፈጻጸም ሂደት፣ ያሣተፈው የኢንተርፕራይዝ ብዛት፣ በኢንትረፕራይዞች አማካኝነት የተፈጠረው የሥራ ዕድል ብዛት፣ ለኢንተርፕራይዙ የፈጠረው ጠቅላላ ገቢ፣ የኮንትራት ስራው/ፕሮጀክቱ ጠቅላላ ዋጋ፣ በስራ ዕድል ፈጠራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ርምጃዎች ወዘተ መያዙን ማረጋገጥ ይገባል፤ አለበት፡፡

(ሐ) ዝርዝር ሪፖርቱ በየተቋማቱ አማካኝነት ለዘርፎች ተጠቃሎ መተላለፍ አለበት፣ ሪፖርቱም በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ በተደራጀ አግባብ መያዝ አለበት፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ ስራዎች አፈጻጸም መረጃ በሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ከዘርፎች ተሰባስቦና በኤጀንሲው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ መሰረት ተዘጋጅቶ ለኤጀንሲው መላክ ይኖርበታል፡፡

(መ) የውል ማቋረጥ ስራ መደበኛውን የኮንትራት አስተዳደር ውል የአሰራር መርህ ሳይጥስ፣ በቅድሚያ ለኢንተርፕራየዙ ሥራው በተገቢው መጠናቀቁን በማረጋገጥ አስፈላጊውን የውል ማቋረጥ ሥነ-ሥርዓት እንደሚከናወን በማሣወቅ ማከናወን መቻል አለበት፤

(ሠ) ኢንተርፕራይዙ በሥራ ሂደቱ እንደ ውሉ ዝርዝር ሁኔታና የሥራ ስፔሲፊኬሽን መሠረት ማከናወን ካልቻለ፤ ህጉ በሚፈቅደውና በኮንትራት ውሉ ስነ ስርአት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በኮርፖሬሽኑ ላይ የደረሰ ጉዳት ካለ ዝርዝሩን በማካተት ኢንተርፕራይዙን ላደራጀው አካል እንዲሁም ለኢንተርፕራይዙ ዋስትና ለሰጠው አካል ሪፖርት መላክ ይኖርበታል፡፡

**ለቋሚ ኢንተርፕራይዞች**

**<u>በኮንትራት ሥራዎችን የመስጠት የሥራ ፍሰት(Sub-contracting)</u>**

ለኢንተርፕራይዞ ሥራን በተቋራጭነት(contracting) ለማስተላለፍ የሚረዳ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

↓

ከአካባቢው የመስተዳደር አካላት ጋር የመቀናጀት ስራ ማከናወን

↓

የኢንተርፕራይዞችን መረጃ የማደራጀት እና የመመዝገብ ስራ

↓

የኢንተርፕራይዞችን መረጃ የማደራጀት፣ መረጣ እና የማጽደቅ ስራ

↓

የተመረጡ ኢንተርፕራይዞችን ወደ ስራ የማስገባት ስራ

↓

ስለ ፕሮጀክቶች ማጠቃለያ ስራ ሪፖርት እና የውል ማቋረጥ ስራ ማከናወን

## ክፍል ስድስት

### 6.1.ለኢንተርፕራይዞች በንዑስ ስራ ተቋራጭነት መስራት ስለሚችሉ ስራዎች

ከሀገራዊ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራተጂ፣የድጋፍ ማዕቀፍና የአፈጻጸም ስልቶች አኳያ ለዘርፉ እድገት ትኩረት ከተሰጠባቸው የኮንስተራክሽን ስራዎች አኳያ በዋነኛነት የንዑስ ሥራ ተቋራጩነት እና የመሰረተ ልማት ግንባታ ንዑስ ተቋራጭነት ኮርፖሬሽኑን በቀጥታ የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም ከሁሉም ዓላማ አስፈጻሚ ዘርፎች በተሰባሰበው መረጃ መሰረት የሚከተሉት ለወጣት ስራ ፈላጊ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንደአግባብነቱ አውትሶርስ የሚደረጉ ናቸው፡፡

1) ***ከትራንስፖርት መሰረተ ልማት ዘርፍ ሥራ አኳያ***

| ተ.ቁ | **በመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት** | የሚፈጠረው የስራ ዕድል የሙያ ስብጥር/ዓይነት | የሥራው አካባቢ |
|---|---|---|---|
| 1 | የፓይል ፋውንዴሽን ሥራዎች | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 2 | ለድሬኔጅ እና ለከልቨርት የሚሆኑ ፓይፖችን ማምረት (PIPE PRODUCTION FOR DRAINAGE & CULVERT WORKS) | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 3 | የአፈር ቁፋሮና ድልዳሎ ስራዎች | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 4 | ቆረጣ የተደረገባቸው የመንገዱ ክፍሎች በሳር የመሸፈን ስራዎች | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 5 | የዲች ስራዎች | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 6 | የፕሮጀክት ኳሪ ሳይትና የድንጋይ ካብ አካባቢ የዛፍ ችግኝ የመትከል ሥራዎች | ግብርና | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 7 | ደቃቅ ጠጠር ስራዎች(FINE PRODUCTION ) | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 8 | የሳይት ኢንቨስትጌሽን ሥራዎች | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| | **በመንገድ ጥገና ፕሮጀክት** | | |
| 9 | ለድሬንጅ እና ለከልቨርት የሚሆኑ ፓይፖችን ማምረት(pipe production for drainage & culvert works) | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 10 | ፉካ የማጽዳት ቁጥቋጦ የማስወገድ ሥራዎች( culvert and bush cleaning) | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 11 | የግንብ ጥገና ሥራዎች (mortar & dry masonary repair) | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 12 | የፍሳሽ ቦይ ሥራዎች (ditch clearing) | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 13 | የእግረኛ ወንገድ ወለል ንጣፍ ማምረት | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |

2) ከህንጻ ቴክኖሎጂና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ስራዎች አኳያ፡- ከህንጻ ግንባታና ተያያዥነት ስራዎች አኳያ

| ተ.ቁ | የስራው አይነት | የሥራ ዋጋ | የሚፈጠረው የስራ ዕድል የሙያ ስብጥር/ዓይነት | የሥራው አካባቢ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የብሎኬት ግንባታ ስራ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 2 | የልስን ስራዎች | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 3 | የፍሳሽ መከላከያ ኮፒንግ እና ፍላሺንግ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 4 | የወለል ስክሪድ ስራ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 5 | የመስኮት ማርብል ሲል | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 6 | ቀለም ስራ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 7 | ኳርትዝ ቀለም ሥራ(ለውጭ ግድግዳ) | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 8 | የሳኒተሪ መስመር ዝርጋታ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 9 | የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 10 | አሉሚኒየም ሥራ | " | የአሉሚኒየም ስራ | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 11 | የማጠናቀቂያ ቦርድ ገጣሚ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 12 | የኮርኒስ ቦርድ ገጣሚ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 13 | አርምስትሮንግ ኮርኒስ ገጣሚ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 14 | ሴራሚክ ፕላስቲክ ንጣፍ ስራ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 15 | ፐርኬ የመሬት ንጣፍ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 16 | ጫኝና አውራጅ | " | ጫኝና አውራጅ | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 17 | አናጢ | " | አናጢ | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 18 | የብረት ማጠፍ መቁረጥ እና ማስቀመጥ ስራ | " | ፌራዩ | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 19 | የፎርምዎርክ ስራ | " | አናጢ | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 20 | የጂብሰም ብሎክ ግድግዳ ሥራ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 21 | የወለል ኮንክሪት ሊሾ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 22 | መስታወት ገጠማ ሥራ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 23 | የበርና የመስኮት ስራ | " | በያጅ | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 24 | የቴራዞና ስራ | " | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ፕሮጀክቶች |
| 25 | የእንጨት በር ገጠማ ስራ | “ | አናጢ | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 26 | የእብነበረድ ግራናይት trade and riser ንጣፍ ስራ | “ | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 27 | የብረት ከንች ስራ | “ | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 28 | የቁፋሮ ስራ | “ | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 29 | የኮንክሪት አርማታ ስራ | “ | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 30 | scaffolding ስራ | “ | አናጢ | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 31 | ጎረንዳዮ ስራ | “ | ጎረንዳዮ | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |
| 32 | የኮብልስቶን ስራ | “ | ኮንስትራክሽን | ሥራው ባላቸው ፕሮጀክቶች |

## *3) ከውሃ መሰረተ ልማት ዘርፍ ሥራዎች አኳያ*

1) የዋና ቦይ መከላከል ሥራ፣
2) የግንብ ሥራ
3) የስዌሬጅ ሥራ
4) የፓይፕ ዝርጋታ
5) ልዩ ልዩ የቁፋሮ ስራዎች ናቸው፡፡

## 4) ከኮንስትራክሽን ማሽነሪና ማንጅመንት ስራዎች አኳያ

1) የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችን ማጽዳት፣መጠገን፣
2) የመለዋወጫ እቃዎችን ማውረድ መጫን፣
3) አነስተኛ የተሽከርካሪ ጥገናችንዎችን መስራት፣
4) በቢሮ አካባቢ የሚኖሩ ልዩ ልዩ የጥገና ስራዎችን መስራት፣

በአጠቃላይ እነዚህንና የመሳሰሉትን ሥራዎች ለወጣት ስራ ፈላጊዎች በየአመቱ በታቀደ አግባብ ለኢንተርፕራይዞች አውትሶርስ በማድረግ ሥራዎች እንዲከናወኑ ማድረግ ይገባል፡፡ አፈጻጸሙም ከዚህ ጋር በአባሪ በተያያዘው ቅጽ መሰረት በማቀድ በዚህ ትይዩ ሪፖርት ማድረግ ይጠይቃል፡፡

### 6.2. የኢንተርፕራይዞች የስራ ዋጋን በሚመለከት

የኢንተርፕራይዞች የስራ ዋጋ እንደወቅቱ ሁኔታ፣እንደአካባቢው እና የስራው አይነት እንደሚለያይ የሚጠበቅ ሆኖ ቀጣይ ኮርፖሬሽኑ የሚያወጣው የአካባቢ እና የስራው አይነት ቁርጥ ዋጋ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### 6.3. የቋሚ ኢንተርፕራይዞች ዋስትና ማቅረብን በሚመለከት

በማናቸውም መንገድ የስራ እድል የሚፈጠርላቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ወይም ግለሰቦች የሚሰጡ ማናቸውም ስራዎች በኮርፖሬሽኑ የአሰራር መመሪያን በማይጥስ መልክ ሆኖ በሀገር ደረጃ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለመደገፍ ከወጡ አሰራሮች ጋር በተዘመደ አግባብ የስራ እድል እንዲፈጠር ምልመላ ያከናወነው አስተዳደር ጋር በመመካከር የሚተግበር ይሆናል፡፡

## *ክፍል ሰባት*

## *7.የአስፈፃሚ አካላት እና ሚናዎቻቸው*

### *7.1. ዋና ዋና አስፈፃሚ አካላት*

በሀገሪቱ የወጣትና ሴቶች ልማት ፖሊሲ አኳያ የሥራ ዕድል ፈጠራን የማስተግበር፣ የማስተባበርና የማሣካት ሥራ የበርካታ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው፡፡ በመሆኑም ከኮርፖሬሽኑ ውጭ ያሉ አካላት ሚና በፖሊሲውና በእስትራተጂው ላይ እንደተመለከተው ይሆናል፡፡ ሆኖም ከኮርፖሬሽኑ የሥራ ባህሪና የግዙፍ ፕሮጀክቶችን ከማንቀሣቀስ አኳያ እና ለወጣቶች የስራ እድል በመፍጠር ከኮርፖሬሽኑ ጋር የተጠናከረ ግንኙነት ያላቸውን አካላት ብቻ በዚህ ማንዋል ለማካተት ተሞክሮአል፡፡ እያንዳንዱ የኮርፖሬሽኑ አመራር እና ሰራተኛ ከባለድርሻ አካላት የሚጠበቁ ስራዎችን በሚመለከት ከዚህ ማነዋል ላይ የተመለከተውን የስራ ድርሻ ታሳቢ በማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡

*(ሀ) በኮርፖሬሽኑ የወጣቶች የስራ እድል ፈጠራ ስራ ላይ ሚና ያላቸው ዋና ዋና አካላት*

1. የኮርፖሬት የሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ
2. የኮርፖሬሽኑ ዓላማ አሥፈፃሚ ዘርፎች

3. የተለያዩ ፕሮጀክትቶች የሚያስፈፅሙ አካላት(ፕ/ጽ/ቤቶች)

4. በተለያዩ አካባቢ የሚገኙ የአስተዳደር አካላት (የአንድ ማዕከልን ጨምሮ)

5. የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ናቸው፡፡ ስለሆነም በዚህ ማንዋል መሰረት የኮርፖሬሽኑ አመራሮችና ባለሙያዎች ተቋማቱ ካላቸው ሚና አኳያ ማከናወን ስለሚገባቸው ተገባራት በዝርዝር ተመላክቷል፡፡

*(ለ) የዋና ዋና አካላት ሚናቸው፡-*

*1. የኮርፖሬት የሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ*

ከዚህ መመሪያ አንጻር የኮርፖሬሽኑየሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፡-

1) የኮርፖሬሽኑን የሥራ ዕድል ፈጠራ አሠራር ወጥ በሆነ አግባብ እንዲፈፀም ዝርዝር የአሰራር ማንዋል ያዘጋጃል፣ ያስጸድቃል፣ ኦረንቴሽን ይሰጣል፣ በዚሁ አግባብ እንዲፈፀም ይከታተላል፡፡

2) የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራ ፕሮግራም በእቅድ እንዲመራ አስቀድሞ ዝግጅት እንዲያደርጉ በኮርፖሬሽኑ ስር ለሚገኙ ዘርፎች፣ፕሮጀክቶች፣ዲስትሪክቶች፣መምሪያዎች ያሣውቃል፤

3) የተጠቃለለ የስራ እድል ፈጠራ እቅድ በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ይልካል፡፡

4) የኮርፖሬሽኑ ሜጋ ፕሮጀክቶች በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ አግባብ ለወጣቶችና ሴቶች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችል ሁኔታ እንዲፈጠር የተለያዩ ሥልቶችን ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ይዘረጋል፣ በአግባቡ እንዲተገበር ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

5) ወጣቶችና ሴቶች ኮርፖሬሽኑ በዘረጋው የአሠራር ሥርአት መሠረት በቀጥታ ተሣታፊና ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ በጥብቅ ዲሲፕሊን እንዲመራ በየግዜው የሚመለከታቸውን የማሳሳብ ስራ ይሰራል፡፡

6) የስራ እድል ፈጠራ አፈጻጸም ሪፖርት ከሁሉም ፕሮጀክቶች፣ዲስትሪክቶች፣ዘርፎች እና መምሪያዎች ለመምሪያው እንዲላኩ አስፈላጊው ክትትል ያደረጋል፡፡ የተጠቃለለ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡ ለሚመለከተው ሁሉ በወቅቱና በተቀመጠው ያሰራር ስርአት መሰረት ሪፖርት ያደርጋል፡፡

7) ሌሎች ከስራ እድል ፈጠራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስራዎች ያከናውናል፡፡

### 2.ዓላማ አስፈፃሚ ዘርፎች ሚና

በዚህ መመሪያ መሠረት የኮርፖሬሽኑ አላማ አስፈፃሚዎች የትራንስፖርት፣ የውሃ መሠረተ ልማት ዘርፎች እና የህንፃና ቴክኖሎጂ ኮንስትራክሽን ዘርፍ ሲሆኑ የግድብና መስኖ አስተዳደር ስርአትን ከዚህ መመሪያ አኳያ ሊያካትት ይችላል። ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በኃላፊዎቻቸው በኩል የሚኖራቸውም ሚናም የሚከተለው ነው፡-

1) በየበጀት ዓመቱ ለወጣቶችና ሴቶች በውክልና ወይም በቀጥታ በማስተላለፍ ወይም በጊዜያዊ ጥቅር መንገድ የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎችን በዝርዝር በመለየት የማቀድ፣ የማሣወቅ፣

2) የተዘጋጀውን እቅድ ለኮርፖሬሽኑ የስትራቴጂክ ማኔጅመንትና እቅድ መምሪያ የማስተላለፍ ስራ ይሰራሉ፣

3) የሥራ ዝርዝሩን መሠረት ያደረገ ተገቢውን የድርጊት መርሃ ግብር የማዘጋጀት፤

4) ዝርዝር ዕቅድና የድርጊት መርሃ ግብሩን በተዋረድ መዋቅሩ መሠረት የማስተላለፍ፣

5) በዘርፍ ደረጃ ለስራ ፈላጊ ኢነተርፐራይዞችወይም ግለሰቦች ስራዎች ሲኖሩ በአቅራቢያው ለሚገኘው የአስተዳደር አካል ዝርዝር የፍላጎት መግለጫ በማዘጋጀት በጽሁፍ የማሳወቅ፣ጥሪ የማድረግ፣እንደአግባብነቱ ለአስተዳደር አካሉ ኦረንቴሽን የመስጠት፣መመዘኛ የማዘጋጀት፣የመላኪያ ግዜ የመወሰን፣ወዘተ ስራዎችን ይሰራል፤

6) ከላይ በተገለጸው ሂደት ከአስተዳደር አካል ለሥራ ዕድል ፈጠራ ተመልምለው የመጡትን ሥራ ፈላጊዎች በመመዘኛው መሠረት የማጣራት፣ የማፅደቅና ውጤቱን ለሚመለከተው አካል የማሣወቅ ኃላፊነት አለበት፣

7) የዘርፍ መ/ቤቶች የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ወይም ባለሙያዎች ለተመረጡ ስራ ፈላጊዎች የሥራ ኦረንቴሽን የመስጠትና በሂደቱ ብቁ የሆኑትን የመለየት ሥራ መሥራት፣

8) የዘርፍ መ/ቤት ኃላፊዎች ወይም ወኪሎቻቸው ብቁ ከሆኑ ኢንተርፐራይዞች እንደአግባብነቱ የሥራ ማስተላለፍ (Outsourceing) ውል መዋዋል ወይም የሽያጭ ውክልና መስጠት ወይም ጊዜያዊ ቅጥር እንዲካሄድ የማድረግ ሥራ መሥራት መቻል አለባቸው፣

9) በዘርፍ ደረጃ ወይም በተዋረድ መዋቅሩ አማካኝነት ለወጣቶች የተፈጠረ የሥራ ትስስር ዝርዝር ሪፖርት ያዘጋጃል ለዋናው ጽ/ቤት በየወሩና በየሩብ ዓመቱ መለክ ይኖርባቸዋል፤

10) በራሱ ደረጃና በስሩ በሚገኙ ተዋረድ መዋቅር የወጣቶችና የሴቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

11) ከላይ ከተገለፁት ዋና ዋና ሥራዎች ባሻገር ለዚህ የአሰራር መመሪያ አፈፃፀም ስኬት መከናወን የሚገባቸውን ዝርዝር የአሰራር ስርአት ሊያዘጋጅ ይችላል፤ ሌሎች ከስራ እደል ፈጠራ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ሥራዎች የማከናወን ኃላፊነት አለበት፡፡

(*ሐ)ግዙፍ ፕሮጀክቶችን የሚያስፈፅሙ ጽ/ቤቶች/ዲስትሪክት ጽ/ቤቶች*

*1)* ለወጣቶችና ሴቶች መተላለፍ የሚችሉ ሥራዎችን በዝርዝር የመለየት ሥራ መሥራት፣

2) ዝርዝር ሥራዎችንም መሠረት በማድረግ መሠማራት የሚችሉ የኢንተርፕራይዞች ዓይነት፣ ብዛት፣ ሥራው የሚፈጀው ጊዜ ዝርዝር መመዘኛዎችን ወዘተ ያዘጋጃል፣

3) መረጃዎችን መሠረት በማድረግም ዝርዝር የማስፈፀሚያ ዕቅድና የድርጊት መረሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ለማዕከል ይልካል፣ ያስጸድቃል፤

4) የተዘጋጀውን ዕቅድና የድርጊት መረሃ ግብር መሠረት በማድረግ ከአካባቢው የአስተዳደር አካል ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፡፡ የጋራ መግባባት ይደርሣል፤

5) ለአካባቢው የአስተዳደር አካል በፅሁፍ የሥራ ዕድል ፈጠራ ትስስር ጥሪ ያስተላልፋል፣

6) የወጣቶች ተሣታፊነትና የአሰራር ግልጸኝነት መርህን በተከተለና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ኢንተርፕራይዞች ወይም ግለሰቦች እንዲመለመል የበኩሉን ስራ ይሰራል፤

7) ስኬታማ የስራ እድል ፈጠራ ለማከሄድ ከአስተዳደር አካሉ የተላከለትን ስራ ፈላጊ በመመሪያው መሠረት በኮሚቴ የማፅደቅና ወደ ሥራ የማስገባት ሥራ መሠራት፣

8) ዝርዝር ሪፖርት በቀጥታ በወርና በሩብ ዓመት ለዋናው መ/ቤት ማስተላለፍ አለበት፡፡

### (መ). የኮርፖሬሽኑ አመራሮች የስራ እድል ከመፍጠር የሚስፈለጓቸው ቅንጅታዊ አሰራሮች

በየደረጃው የሚገኙ የኮርፖሬሽኑ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ማንዋሉን ተፈጻሚ ከማድረግ አኳያ የሚመለከታቸው አካላት የሚኖራቸውን ሚና በዝርዝር በማወቅ መፈጸምና ለስኬቱ ማስተባበር የሚገባቸው ነው፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት አካላት የሚኖራቸው ሚና የሚከተለው ነው፡፡

### 1/ ከአስተዳደር አካላት (በከተማ የአንድ ማእከል አገልግሎት) የሚኖር ቅንጅታዊ አሰራር፡-

የአስተዳደር አካላት በገጠርም ሆነ በከተማ አካባቢ የሚገኙና በወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራ ላይ ቀጥተኛ ተልዕኮ ያላቸውን የሚመለከት ነው፡፡ ዝርዝር ተግባራቸው በሌሎች የስራ እድልና የምግብ ዋስትና የአሰራር መመሪያዎች እንደሚሸፈን ግምት ገብቶ የኮርፖሬሽኑን የስራ እድል ፈጠራና የአንድ ማእክል አገልግሎት አሰራርን በተገቢው ከመጠቀም እና ከማሳለጥና የስራ እድል የሚፈጠርባቸው አመራሮችና/ባለሙያዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት የሚኖራቸው ዋና ዋና ተግባራት፡-

1) ከማዕከል/ከዘርፍ/ ከዲስትሪክት ጽ/ቤት ወይም ከፕሮጀክት ጽ/ቤቶች የሚተላለፍበትን የሥራ ትስስር ዕድል ለአካባቢው ሥራ ፈላጊዎች በግልጽ እንታወቅ የማደረግ ስራ እንደሰራ ማደረግ ስራ ይሰራል፣ የሥራ ሂደት አመቻቹ እንዲሳተፍበት ያስደርጋል፡፡

2) ከሥራ ፈላጊዎች መካከል በአመቻቹ አማካኝነት የኮርፖሬሽኑ አመራር ባስተላለፈው መመዘኛ ማሟላት የሚችሉት እንዲመለመሉ ይከታተላል፡፡ በዚህም ወቅትም የኮርፖሬሽኑ ባለሙያ በታዛቢነት እንዲገኝ ከሚመለከተው ኃላፊ ጋር ይሰራል፤

3) የተመለመሉትን ሥራ ፈላጊዎችን በአመቻቹ አካል በፅሁፍ ለውድድር እንዲቀርቡ በሚመለከተው ኃላፊ በጽሁፍ እንዲተላለፍ ያስደርጋል፡፡ ደብዳቤው ዝርዝር የውሣኔ ሃሣብ በቃለ-ጉባዔው መያያዙን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል፣

4) ከተላኩ ሥራ ፈላጊዎች በመመዘኛው መሠረት የማጣራትና የማፅደቅ ሥራ ያከናውናል፡፡ በወቅቱም የአስተዳደሩ ተወካይ በታዛቢነት እዲገኝ ያስደርጋል፡፡

5) በተለያየ ምክንያት የሚንጠባጠቡ፣ ወይም እንደውሉ መፈፀም የማይችሉ ኢንተርፕራይዞች በሚኖሩበት ወቅት ተተኪ ኢንተርፕራይዞችን በአስተዳደሩ በበኩል እንዲላክ ያስደርጋል፣

6) ሌሎች ለዚህ የሥራ ዕድል ፈጠራ የአሠራር ማንዋሉ ስኬት አሥፈላጊ የሆኑ ተግባራትን በቅንጅት ያከናውናል፡፡

## 2/*ከፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ጋር ለመቀናጀት የሚኖራቸው ዋና ዋና ተግባራት፡-*

1) የኮርፖሬሽኑ ተቋማት ባለሙያዎችና አመራሮች በሥራ ዕድል ፈጠራ ስራ አሰራር ላይ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት እንዲቻል የተላያዩ ስጠናዎች እንዲሰጡ ለኤንሲው ጥያቄዎችን ማቅረብ እና አፈጻጸሙን መከታተል ስራ መስራት፣
2) በበጀት አመቱ ኮርፖሬሽኑ በሚያዘጋጀው የስራ እድል ፈጠራ ዕቅድና ወርሃዊም ሆነ የሩብ አመት፣ግማሽ አመት አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ተገቢው ግብረ መልስ እንዲሰጠበት አስፋጊውን ጥያቄ ማቅረብ፣በግብረመልሱ መሰረት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣
3) በቀጣይነትነት የሚኖሩ ለውጦችን ለማስገንዘብ እንዲረዳ ስለ ሪፖርት አቀራረብ ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት ለውጦች ወይም ቅፃቅፆችን ለኮርፖሬሽኑ እንዲያሳውቁ ተገቢውን የስራ ግንኙነት ማድረግ፣ወኪል እንዲመደብ መጠየቅና በዚሁ አግባብ እንዲፈጸም የመከታተል፣የማሣወቅ ሥራ መስራት፣
4) የኮርፖሬሽኑ የሴቶች፣ህጻናትና ወጣቶች መምሪያና ስትራተጂክ እቅድ መምሪያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መነገድ ከኤጅነሲው ጋር በትብብር መስራት፣ከላይ የተመለከቱ ስራዎች እንዲሳኩ በኃላፊነት መንፈስ መስራት ይገባል፡፡

## *7.2. አጠቃላይ የስራ እድል ፈጠራ አሰራር የክትትልና ግምገማ ሥርዓት፡-*

የኮርፖሬሽኑ የስራ እድል ፈጠራና የአንድ ማእከል አገልግሎት ከላይ በዝርዝር መመልከት እንደሚቻለው በየደረጃው በሚገኘው አመራር በሪፖርት፣በሱፐርቪዝን እና በአጠቃላይ የስራ አፈጸጸም ግምገማ የሚከናወን ይሆናል፡፡ በመሆኑም አጠቃላይ የግምገማና ክትትል ስራ በኮርፖሬሽን ደረጃ በሚከተሉት መንገዶች የሚፈጸም ይሆናል፡፡

### 1/ ሪፖርት አቀራረብ ስርአት፡-

ኮርፖሬሽኑ የስራ እድል ፈጠራን በሚመለከት የወር፣የሶስት ወር፣የስድስት ወርና የአመት ስራ አፈጸጸምን የሚመከለት ለዋናው መስሪያ ቤት ተልእኮ በየጊዜው እየታየና ግብረ መልስ

እየተሰጠ የሚመራበት ስርአት ይኖረዋል፡፡ ዝርዝር ሁኔታውም በሚከተለው አግባብ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

1) የሥራ ፈላጊዎችን በዕቅድና በፕሮግራም መምራት እንዲቻል ፕሮጀክቶች ለዘርፍ፣ዘርፎች ለማዕከል ዝርዝር የሥራ አፈፃፀምን አስመልክቶ ከኮርፖሬት የሴቶች፣ህጻናት እና ወጣቶች መምሪያ ይቀርባል፡፡ የተጠቃለለው ለስትራተጂክ ማኔጅመንትና እቅድ መምሪያ በየወሩ እና በየሩብ ዓመቱ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት ሪፖርት የማስተላለፍ ሥራ መሠራት አለበት፡፡
2) የኮርፖሬሽኑ የስትራተጂክ ማኔጅመንትና እቅድ መምሪያ ከሴቶች ህጻናት ወጣቶች መምሪያ፣ የመደበኛ ሪፖርቶች ከዘርፎች እና መምሪያዎች የተላከውን ሪፖርት /መረጃ/ በዝርዝር በመገምገም የተጠቃለለ ሪፖርት ለመንግስት የልማት ድርጅቶችና እንደአግበባነቱ ለከተሞች የስራ እድል ፈጠራና ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በየሩብ ዓመቱ ይላካል፡፡
3) ማናቸውም የስራ እድል ፈጠራ ሪፖርቶች የሚላኩት ከዚህ ጋር በአባሪ በተያያዘው ቅጽ መሰረት ሆኖ በአባሪነት ዝርዝር መግለጫ የያዘና ግምገማዊ የሆነ መሆን አለበት፡፡ ማለትም የነበረው የስራ እቅድ እቅድና አፈጻጸም ደረጃ በሚለካ መንገድ፣የተገኘው ውጤት፣ በእቅድ አፈጻጸም ሂደት የነበሩ ስኬቶችና ውድቀቶች ዋነኛ ቁልፍ/ገዥ ምክንያቶች፣የቀጣይ አቅጣጫና የአመራር ሚና በጥንካሬም ሆነ በእጥረት በሚያስገነዘብ ሆኖ የቀጣይ ተስፋን አመላካች እንዲሆን በሪፖርቱ እንዲካተት ማደረግ ይገባል፡፡

## *2/ የክትትልና እና ሱፐርቪዝን ስራ አፈጻጸም ስርአት*

1) የክትትልና ድጋፍ ሥራ መሰራት ያለበት ቀደም ሲል በተዘጋጀ የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፤
2) የኢንተርፕራይዙ የየእለት የሥራ እንቅስቃሴ ሁኔታ በየቀኑ በስራው አካባቢ በሚገኘው የኮርፖሬሽኑ ተወካይ ባለሙያ አማካኝነት ክትትል ይደረጋል፣ከሚመለከታቸው ጋር መረጃ ይለዋወጣል፤
3) የኮርፖሬሽኑ ወይም የስራ ዘርፉ ወይም ስራውን የሰጠው ተቋም ተወካይ የኢንተርፕራይዞችን የሥራ አፈፃፀም ሂደት በየሣምንቱ አንድ ጊዜ ክትትል በመስክ ደረጃ ያካሄዳል፤አጭር የጽሁፍ ሪፖርት እያቀረበ ያስገመግማል፡፡ እንደአግባነቱ

የሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላት እንዲሳተፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህንን ማድረግ ባልቻለ ወቅትም የግምገማ ውጤት ሪፖርት ለሚመለከተው የቅርብ የአስተዳደር አካል ያስተላልፋል፡፡

4) ኮርፖሬሽኑ በዋናኘነት በሶስት ወር አንድ ግዜ ከማእከል ቡድን በማደራጀት የሱፐርቢሽን ስራ ይሰራል፡፡ በየመስኩ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡ ተግባሩም በዝርዝር እቅድ እየተዘጋጀ የሚተገበር ይሆናል፡፡

5) በተመሳሳይ ዘርፎች፣የዲስትሪክት ጽ/ቤት ኃላፊዎችና የፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊዎች በመስክ በመገኘት አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ እንዲያድርጉ አቅጣጫ ይሰጣል፡፡ ቢያንስ በየሁለት ወር እንዲፈጸም የሚያስችል ስራ ይሰራል፡፡ አስፈላጊው ሪፖርት ለኮርፖሬሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚና ለሚመለከተው መምሪያ እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡

3/ ግምገማ

1) የሥራ ፈላጊዎች የሥራ አፈፃፀም ሂደት በየዕለቱና በሣምንት አንድ ቀን ስራው ባለበት ፕሮጀክቶች አካባቢ ወይም ዘርፍ የቃልና የፅሁፍ ሪፖርት እየቀረበ ይገመገማል፡፡
2) ዘርፎች ከዲስትሪክቶች የሚቀርቡ የሥራ ፈላጊዎችን ሪፖርት በዝርዝር በየወሩ ይገመግማሉ፣ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ/ ሪፖርትም ለሚመለከተው ዋና መ/ቤት መምሪያዎች ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡
3) ማዕከል ለዝርዝር ግምገማ እንዲረዳ ለናሙና በየሩብ አመቱ የሚሆን ቢያንስ አንድ ጊዜ የሱፐርቪዥን ሥራ ይሰራል፤በመስክ ይገመግማል፣ ከየፕሮጀክትና ከየዘርፍ በሩብ ዓመት የቀረበውን ሪፖርት መሠረት በማድረግ ይገመግማለ፤ የቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

4) እንደአግባብነቱ የስራ እድል ፈጠራውን በሩብ አመት/ግማሽ አመት ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር በመቀናጀት ይገመግማል፡፡ የጋራ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

## *ክፍል ስምንት*

## *ልዩ ልዩ ጉዳዮች*

### *8.1. በኢንተርፕራዞች ስለሚቀርብ ቅሬታ*

በኢንተርፕራይዞች የሚቀርብ ማናቸውም ቅሬታ በኮርፖሬሽኑ የአቤቱታና ቅሬታ አፈታት ማንዋል መሰረት የሚፈታ ይሆናል፡፡

### *8.2. ስለተከለከሉ ተግባራት*

1) በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የኮርፖሬሽኑ ተቋም በዚህ መመሪያ መሰረት ለነባር ኢንተረፕራይዞች ከሁለት ግዜ በላይ የስራ እድል እንዲፈጠር ማድረግ አይችልም፡፡

2) ማንኛውም የኮርፖሬሽኑ ተቋም ሙያ በማይፈልጉና በአካባቢው የህብረተሰብ ክፍል መሰራት የሚችሉ ስራዎችን ከሌሎች አካባቢ ግለሰቦችን ወይም ኢንትረፕራይዞችን በማምጣት ስራዎችን ማስተላለፍ አይችልም፡፡

3) በሽርክና ወይም በኅብረት ስራ ማህበር በመደራጀት ሊተገበሩ የሚችሉ ስራዎችን ከሚመለከተው የባለድርሻ አካል ጋር ሳይቀናጅ ለግለሰቦች ስራዎችን ማስተላፍ የተከለከለ ነው፡፡

### 8.3.የአሰራር ማንዋሉ ስለሚጸናበት ግዜ

ይህ የአሰራር መመሪያ የኮርፖሬሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ ለሚመለከታቸው ካስተላለፉበት ወር ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

### *8.4. ማንዋሉን ስለማሻሻል*

ይህ የአሰራር መመሪያ ከህግና ከአሰራር ተቃራኒ ሆኖ ሲገኝና በተግባር ማስፈጸም የማያስችል ሁኔታ ሲፈጠር በኮርፖሬሽኑ ዋና ስራ አስፈጻሚ አማካኝነት ሊሻሻል ይችላል፡፡

# የዕቅድና ሪፖርት ማቅረቢያ

# አባሪዎች

# የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን

## የ ወር 2012 ዓ.ም በቀጥታ ቅጥር የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች

| የስራ ዕድል ፈጠራ በክልል እና በፕሮጀክት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ፕሮጀክቱ የሚገኝበት ክልለ | ልዩ ቦታ/ፕሮጀክቱ/ | የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች | | | | | | | | | ሥራ ከተፈጠረላቸው ውስጥ ወጣት | | | | | | ስራ ከተፈጠረላቸው ውስጥ ምሩቃን | | | | | | ጠቃላላ የተፈጠረ የሥራ ዕድል | | | | | |
| | | | ቋሚ | | | ኮንትራትና ጊዜያዊ | | | ድምር | | | ቋሚ | | | ኮንትራትና ጊዜያዊ | | | ቋሚ | | | ኮንትራትና ጊዜያዊ | | | ቋሚ | | | ኮንትራትና ጊዜያዊ | | |
| | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 1 | አዲስ አበባ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | ኦሮሚያ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3 | አማራ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 4 | ትግራይ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 5 | ደቡብ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6 | ድሬደዋ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7 | ሀረር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 8 | ቤ/ጉምዝ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9 | ጋምቤላ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 10 | አፋር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 11 | ሶማሌ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ድምር | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

- ወጣት ማለት በሀገሪቱ ፖሊሲ መሰረት እድሜው ከ15-35 የሆነ ነው፡፡

የ ወር 2012 ዓ.ም በሰብ ኮንትራት/Subcontracting) የስራ እድል በኢንተርፕራይዝ የተፈጠረላቸው ዜጎች

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ | ልዩ ቦታ/ፕሮጀክቱ/ | የስራው አይነት | የኢንተርፕራይዝ ብዛት | ጠቅላላ የኢንተርፕራይዝ አባላት ብዛት | | | ስራ ከተፈጠረላቸው ውስጥ ምሩቃን | | | የተፈጠረው ዋጋ በብር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | | |
| 1 | አ/አ | | | | | | | | | | | |
| 2 | ኦሮሚያ | | | | | | | | | | | |
| 3 | አማራ | | | | | | | | | | | |
| 4 | ትግራይ | | | | | | | | | | | |
| 5 | ደቡብ | | | | | | | | | | | |
| 6 | ድሬደዋ | | | | | | | | | | | |
| 7 | ሀረር | | | | | | | | | | | |
| 8 | ቤ/ጉምዝ | | | | | | | | | | | |
| 9 | ጋምቤላ | | | | | | | | | | | |
| 10 | አፋር | | | | | | | | | | | |
| 11 | ሶማሌ | | | | | | | | | | | |
| | ድምር | | | | | | | | | | | |

ማሳሰቢያ፡- በየፕሮጀክቱ የኢንተረፕራይዙ መረጃ ይያዛል፡፡ በስራ ዕድል ፈጠራ መመሪያ መሰረት አንድ ኢንተርፕራይዝ ሁለትና ከዚያ በላይ አባላት ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህ የአሰራር ትይዩ መሰረት እቅድ ይታቀዳል፡፡

**<u>የ          ወር 2012 ዓ.ም በሽያጭ ውክልና በመስጠት የተፈጠረ የስራ እድል</u>**

| ተ.ቁ | ክልል/ከተማ | ልዩ በታ/ፕሮጀክቱ/ | የስራው አይነት | የውክልናመጠን በገንዘብ | የተወካይ ኢንተርፕራይዝ ብዛት | የተወከሉ አባላት ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ወ | ሴ | ድምር |
| 1 | አ/አ | | | | | | | |
| 2 | ኦሮሚያ | | | | | | | |
| 3 | አማራ | | | | | | | |
| 4 | ትግራይ | | | | | | | |
| 5 | ደቡብ | | | | | | | |
| 6 | ድሬደዋ | | | | | | | |
| 7 | ሀረር | | | | | | | |
| 8 | ቤ/ጉምዝ | | | | | | | |
| 9 | ጋምቤላ | | | | | | | |
| 10 | አፋር | | | | | | | |
| 11 | ሶማሌ | | | | | | | |
| | ድምር | | | | | | | |

ማሳሰቢያ፡- በስራ ዕድል ፈጠራ ማንዋሉ መሰረት አንድ ኢንተርፕራይዝ ሁለትና ከዚያ በላይ አባላት ያላቸው ናቸው፡፡በዚህ የአሰራር ትይዩ መሰረት እቅድ ይታቀዳል፡፡